ማን ይናገር የነበረ...

# የታኅሣሡ ግርግርና መዘዙ

# AAUP BOOKS CURRENTLY IN PRINT

- የሐረግ አደማሱ። ፪ሺ፱ ዓ.ም.። የጭራሮ ጉንጉኔ፤ የሕይወቱና የስነጽሑፉ ታሪክ
  ብር 95.00
- Hiwot Tefera, *Tower in the Sky*
  Br. 62.00
- Getachew Desalegn, Melaku Abegaz, Demel Teketay and Alemu Gezahgne *Commercial Timber Species In Ethiopia: Characteristics and Uses*
  Br. 90.00
- Dr. Hirut Terefe. Gender Relation, Female Genital Mutilation and Reproductive Health
  Br. 70.00
- አክሊሉ ደሳለኝ መዝገበ ቃላት እንግሊዝኛ-ትግርኛ
  ብር 92.00
- ማንይንገረው ሸንቁጥ ባለአከርካሪዎች
  ብር 75.00
- Abebe Getahun and Eshete Dejene (Phd) Fishes of lake Tana: A Guide Book
  Br. 42.00
- Alemayehu Geda. *2011 Readings on the Ethiopian Economy*
  Br. 160.00
- ሰሎሞን ይርጋ። ፪ሺ፫ ዓ.ም.። ስለ ብቸኛ ዝርያዎች መንስኤ
  ብር 85.00
- ጸጋዬ ገብረ መድኅን። ፪ሺ፬ ዓ.ም.። የጸጋዬ ገብረ መድኅን ታሪክና ተውኔቶች
  ብር 83.00
- Ian Campbell, 2001. *The Plot to Kill Graziani*
  Birr 91.00
- መንግሥቱ ለማ። 2ሺ3 ዓ.ም.። መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ።
  ብር 50.00
- አጽልዕ ጋርሰሳክ (ተርጓሚ) ተመስገን ደብሬ መኮንን። ፪ሺ፬ ዓ.ም.። የሃበሻ ደብዳቤ።
  ብር 40.00
- ጌታቸው ኃይሌ (ተርጓሚ)። ፪ሺ፬ ዓ.ም.። ደቂቀ እስጢፋኖስ በሕግ
  ብር 65.00
- Demel Teketay. 2010. *Edible Wild Plan In Ethiopia.*
  Br. 100.00
- ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፤ ፪ሺ፬ ዓ.ም.። ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፤ ሥራዎች
  ብር 30.00
- ሊቀ ጉባኤ ፈቃደ ሥላሴ ተፈራ። ፪ሺ፬ ዓ.ም.። ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት አዘገጃጀት
- Biadgelign Ademe. 2010. *General Learning Teaching Methods and Techniques.*
  Br. 70.00
- ልዑል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ። ፪ሺ፬ ዓ.ም.። ካየሁት ከማስታውሰው
  ብር 80.00
- ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ። ፪ሺ፬ ዓ.ም.። ለዓባይ ውሃ ሙግት
  ብር 60.00
- ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ። ፪ሺ፬ ዓ.ም.። ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ፤ ማህበራዊና ሥነ ልቦናዊ ትንተና
  ብር 65.00
- Daniel Kitaw. 2009. *Industrial Management and Engineering Economy: An Introduction to Industrial Engineering Textbook*
  Br. 80.00
- ቴዎድሮስ ገብሬ። ፪ሺ፬ ዓ.ም.። በድኅረ-[illegible] የሥነ ጽሑፍ ንባብ
  ብር 35.00
- ባሕሩ ዘውዴ። ፪ሺ፬ ዓ.ም.። የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847—1983
  ብር 30.00
- Alemayehu Teferra. 2006 *Principles of Foundation Engineering*
  Br. 80.00
- Solomon Tadesse. 2008. *Mineral Resources Potential of Ethiopia.*
  Br. 40.00
- Bahru Zewde. 2008. *Society, State and History: Selected Essays*
  Br. 95.00
- Demissu Gemeda and Seid Mohammed. 2008. *Fundamental Concepts of Algebra*
  Br. 20.00
- Emebet Mulugeta (ed.). 2008. *Urban Poverty in Ethiopia: The Economic and Social Adaptations of Women*
  Br. 15.00
- Andrew J. Carlson and Dennis G. Carlson. 2008. Health, Wealth, and Family in Rural Ethiopia.
  Br. 15.00
- ጌትነት እንየው። ፪ሺ፩ ዓ.ም.። እቴጌ ጣይቱ ታሪካዊ ተውኔት
  ብር 15.00
- ገብረወልድ እንግዳወርቅ። ፪ሺ፩ ዓ.ም.። ማይጨው፤ የማይጨው ዘመቻና የጉዞው ታሪክ
  ብር 15.00
- ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ። ፪ሺ ዓ.ም.። ወዳጄ ልቤ እና ሌሎችም

# Forthcoming

- Ian Campbell, 'The Massacre of Debre Libanos Ethiopia 1937 THE STORY OF ONE OF FASCISM'S MOST SHOCKING ATROCITIES'
- Afework & Yalden, 'Mammals of Ethiopia and Eritrea'

**NB: All prices are at local wholesale rate.**

# ማን ይናገር የነበረ...

# የታኅሣሡ ግርግርና መዘዙ

ብርሃኑ አስረስ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ

፲፱፻፺፮ ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ

ፖስታ ሣጥን ቁጥር፤ 1176

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስልክ፣ ቀጥታ +251-011-123 97 46

ፋክስ፤ +251-011-124 32 91

ኢ-ሜል፤ aau.press@ethionet.et

© አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ፪ሺ፲፭ ዓ.ም.

ISBN 978-99944-52-53-8

የሽፋን ዲዛይን አገኘሁ አዳነ

# ማውጫ


ገጽ

ቀዳሚ ቃል ................................................................................ vii

መግቢያ ................................................................................ xi

## ክፍል አንድ
## የታኅሣሡ ግርግር ለምን ተነሳ?

ምዕራፍ ፩ የታሪኬ አጋጣሚ ................................................................................ 1

ምዕራፍ ፪ ቅድመ ሁኔታ ................................................................................ 21

*ተፈሪ መኮንን* ................................................................................ 21

*የሥልጣን ፉክክር* ................................................................................ 23

*የዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አመሠራረት* ................................................................................ 31

*የአገር ጠባቂ ጦር አመሠራረትና አደረጃጀት* ................................................................................ 41

*ሥርዓቱ የፈጠራቸው ችግሮች ተቃውሞ ስለማስነሳታቸው* ................................................................................ 57

## ክፍል ሁለት
## የታኅሣሡ ግርግር

ምዕራፍ ፫ መፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ................................................................................ 63

*ወርቅነህ ገበየሁ( ?- ፲፱፻፶፫)* ................................................................................ 63

*ገርማሜ ንዋይ (፲፱፻፲፮ - ፲፱፻፶፫)* ................................................................................ 115

*ብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ (፲፱፻፱ - ፲፱፻፶፫)* ................................................................................ 130

ምዕራፍ ፬ የመፈንቅለ መንግሥቱ ጥንስስ ጠቋሚ ሁኔታዎች ................................................................................ 143

ምዕራፍ ፭ ለመፈንቅለ መንግሥቱና በመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ላይ
የተደረጉ ዝግጅቶች ................................................................................ 151

*የክብር ዘበኛ ዝግጅት (ማክሰኞ ታኅሣሥ ፬ ቀን)* ................................................................................ 151

*የመፈንቅለ መንግሥቱ አጀማመር* ................................................................................ 163

*የጦር ሠራዊት የተቃርኖ ዝግጅት* ................................................................................ 175

*የክብር ዘበኛ ቀጣይ ዝግጅት (ረቡዕ ታኅሣሥ ፭ ቀን)* ................................................................................ 179

*የጦር ሠራዊት ቀጣይ የተቃርኖ ዝግጅት* ................................................................................ 194

ምዕራፍ ፮ የመፈንቅለ መንግሥቱ እንቅስቃሴ ................................................................................ 205

*ኮተቤ ላይ የታገደው ጦር (ሐሙስ ታኅሣሥ ፮ ቀን)* ................................................................................ 205

የክብር ዘበኛ ጦር ግዳጅ መደናቀፍ......233
ምስቅልቅል (ዓርብ ታኅሣሥ ፱ ቀን)......239
ንጉሡ ስለ መፈንቅለ መንግሥቱ እንዴት ሰሙ?......244
የቅዳሜው ትግልና ዕልቂት......256
ንጉሡ ከአሥመራ ወደአዲስ አበባ......259
የትግሉ ፍፃሜ......261
ምዕራፍ ፯ የመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ፍፃሜ......263
ጦር ሠራዊቱ የድል ባለቤትነቱን አረጋገጠ (ታኅሣሥ ፰ - ፱)......263

## ክፍል ሦስት

## የታኅሣሡ ግርግር መዘዝ

ምዕራፍ ፰ የመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ የተወው አሻራ......273
ከመፈንቅለ መንግሥቱ ከሽፈት በኋላ በአንደኛ ክፍለ ጦር......273
የአንደኛ ደረጃ ተከሳሾች ፍርድ ቤት መቅረብ......286
የሁለተኛ ደረጃ ተከሳሾች ፍርድ ቤት መቅረብ......294
የወህኒ ቤት ቆይታዬና ትዝታዬ......326
የወህኒ ቤት ቆይታ ትዝብት፣ አርቆ ማቃናት......332
የክብር ዘበኛ ሠራዊት መበተን......348
መፈንቅለ መንግሥቱ ያስፈነው ንቃት......351
ያንዣበበውን ችግር ለመፍታት ታስበው ከነበሩ ሙከራዎች......365
ምዕራፍ ፱ የኑሮ ዕጣዬ......369
ከእሥር ተፈታሁ......369
ጎንደር አካባቢን ለማልማት አንዳንድ አስተዋፅኦ ማድረጌ......376
በአጋዴን የልማት ሥራ አስኪያጅነት......389
በኢዲዲሲየሻምበል (በኋላ የሻለቃ) ካሣዬ አራጋውና
ከሻለቃ መላኩ ተፈራ ጋር......400
አባሪ......430
ምንጭ......442
የቃል መረጃ ሰጪዎች......442
ሰነድ......444
ዋቢ መጻሕፍት......445
ጋዜጦች......445

# ቀዳሚ ቃል

ይህ አቶ ብርሃኑ አስረስ ያቀረቡልን መጽሐፍ ዋነኛው ትኩረቱ በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. የተሞከረው መፈንቅለ መንግሥት ላይ ነው፤ እርሳቸው በቦታው ስለነበሩ፣ ተካፋይም ስለሆኑ፣ ያዩትንና የሰሙትን ትውስታቸውን አቅርበዋል። በመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ላይ ከተካፈሉ ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ ትዝታቸውን በመጽሐፍ መልክ ሲያሰፍሩ፣ አንዳንዶች ደግሞ ለተመራማሪዎች ቃለ መጠይቅ በመስጠት ትውስታቸውን እንዲመዘገብ አድርገዋል። በነዚህ ምክንያቶች ስለሙከራው ሒደት፣ ስለጠንሳሾቹ፣ ስለሌሎቹ ግንባር ቀደም ተዋናዮች እና ከሒደቱ ጋራ ተያያዥ ስለነበሩት ሁነቶች (የተካፋዮቹ የእሥር ሁኔታ፣ የፍርድ ሒደት፣ የሙከራው መዘዝ እና የተለያዩ ጉዳዮች) ያለውን ታሪካዊ ግንዛቤ አስፍረውታል። ስለዚህ፣ አንድ አንባቢ ወይም አንድ ተመራማሪ ይህ አዲስ መጽሐፍ ምን የሚጨምረው ያልታወቀ ነገር አለ ብሎ ቢጠይቅ ተገቢ ይሆናል። በርግጥም፣ *ማን ይናገር የነበረ... የታኅሣሡ ግርግርና መዘዙ* ስለተጨናገፈው መፈንቅለ መንግሥት የማይታወቁ አንዳንድ ጉዳዮችን እንድናውቅ ያደርገናል። ሁሉንም የዚህ መጽሐፍ አስተዋጽኦዎች መዘርዘር ባይቻልም፣ አንዳንዶቹን መጥቀስ አስፈላጊ ይሆናል።

በመፈንቅለ መንግሥቱ ላይ የመጀመሪያውን ጥናታዊ ጽሑፍ በዝርዝር ያቀረበው ሪቻርድ ግሪንፊልድ የተባለ የብሪታኒያ ዜጋ ሲሆን፤ በወቅቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ (በሁዋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ከዚያ ቀጥሎ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) የተማሪዎች ዲን የነበረ ሰው ነበር።[1] ከግሪንፊልድ በሁዋላ አያሌ መጻሕፍትና ምሑራዊ መጣጥፎች ተመራማሪዎችና ተካፋዮች ቢያሳትሙም[2] የግሪንፊልድ መጽሐፍ ዛሬም ቢሆን ከፍ ያለ ጠቀሜታ ያለው ሥራ ነው። ይህ መጽሐፍ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ የቴሌግራሚን ጉዳይ ያነሳው። ይህች ቴሌግራም የተላከችው ከዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሲሆን እርሳቸውም የገርማሜ አዲስ አበባ መቆየት ተገቢ እንዳልሆነና ባስቸኳይ ወደሥራው፣ ማለትም የአውራጃ ገዢ ወደነበረበት ወደጅጅጋ ከተማ እንዲሔድ፣ የሚያዙበት ሰነድ ናት። የዚህችን ቴሌግራም ወሬ ስለሰሙ ወንድማማቾቹ፣ መንግሥቱና ገርማሜ፣ የተሟላ ዝግጅት ባያደርጉም፤ መፈንቅለ መንግሥቱን ለማካሔድ ወሰኑ። ስለዚህ፣

---

1 Richard Greenfield, *Ethiopia: A New Political History* (London: Pall Mall Press, 1965) ይህ መጽሐፍ በጣልያን ጊዜ ስለነበረው የአርበኞች እንቅስቃሴ የሚሰጠው ትረካ እጅግ ጠቃሚ ነው። ከጣልያን በሁዋላ (ከ፲፱፻፴፫ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፶፫ ዓ.ም ድረስ) ያሉት ሁለት አስርት ላይ ሰፊ ትንተናና ገለጻ ያቀርባል፤ ይህም የመጽሐፉን ዋጋ ይጨምራል።

2 ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ሁለት መጻሕፍት ይመለከቷል፡- ኮ/ል ቃለ ክርስቶስ አባይ፣ *የ1953ቱ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራና ከ1908 - 1966 ዓ.ም የኢትዮጵያ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ሂደት* (አዲስ አበባ፣ ፲፱፻፺፯)፤ ይላቅ ኃይለ *ማርያም፣ የሌተናል ኰሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ልዕለ ሥራና የ፲፱፻፶፫ቱ ዓ.ም መፈንቅለ መንግሥት ትክክለኛ ገጽታ (አዲስ አበባ፣ ፲፱፻፺፯)*።

ቴሌግራሚ የተነሳችው፣ ለምን በደንብ ሳይዘጋጁ መፈንቅለ መንግሥቱን ሞከሩ ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነው። ከግሪንፊልድ በሁዋላ ለአያሌ ዘመናት በከሸፈው መፈንቅለ መንግሥት ላይ ምርምር አልተደረገም ነበር፤ ዘመኑ ይኽንን ጉዳይ ለማጥናት የሚያመችም አልነበረም። አብዮት ከፈነዳ በሁዋላ ሁኔታዎች ተቀያየሩ፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ተማሪ የታኅሣሡን ግርግር (መፈንቅለ መንግሥቱ በህዝብ ይጠራበት የነበረ ስም ነው) የድግሪ ማሟያ ጽሑፍ (ቲሲስ ወይም ዲማጽ) አድርጎት ጉዳዩን እንደገና በቅርበት ዓይቶት ነበር፤ ይህም ዲማጽ ያችኑ ቴሌግራም ጠቅሶ ወንድማማቾቹ ሳይዘጋጁበት መፈንቅለ መንግሥቱ ውስጥ የገቡበት ምክንያት ምናልባት በቴሌግራሚ ምክንያት ሊሆን ይችላል በሚል ደምድሟል[3]።

መፈንቅለ መንግሥቱ ውስጥ በመካፈላቸው ለአያሌ አመታት ታሥረው ከተፈቱ በሁዋላ፣ አቶ ብርሃኑ ጉዳዩን ሲከታተሉ ቴሌግራሚን አግኝተዋት ኖሮ፣ በመጽሐፋቸው ውስጥ የፎቶ ግልባጭ ከተዋል፤ በትረካቸውም ውስጥ ይጠቅሷታል። ለመጀመሪያ ጊዜ አንባቢም ያያታል፤ ይልቁንም ዘመኑን የሚያጠኑ የታሪክ ጸሐፊዎች ቀረብ አድርገው እንደሚያተኩሩባት አይጠረጠርም። በዚህ ሁኔታ ይህቺን ሰነድ ሲመዝኗት፣ አንባቢውን የሚያስደምመው ሁኔታ የተላከችበት ጊዜ (ህዳር ፳፱)ና ወንድማማቾቹ መዘዘኛውን እርምጃቸውን የወሰዱበት ጊዜ (ታኅሣሥ ፬) መካከል ያለው ልዩነት ነው። እውነትም እርሷ ከሆነች የነገሩ መነሾ፣ መፈንቅለ መንግሥቱ ከሦስት ወይም ከአራት ቀን በፊት መካሔድ ነበረበት። ስለዚህ፣ የእርሷን መነሾነት ወደጎን አድርገን ሌላ ምክንያት መፈለግ ሊኖርብን ነው። የአቶ ብርሃኑ ትዝታ በዚህ በኩል አይረዳንም፤ ነገር ግን ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያደርገው፣ ወደፊት የሚመጣው ተመራማሪ ለምን በዚያ ቀንና ሰዓት ብርጋድየር ጄኔራል መንግሥቱና ወንድሙ ገርማሜ ነዋይ እዚህ ውስጥ ገቡ የሚለውን ጥያቄ እንደ አዲስ አንስቶ መልስ መፈለግ እንዳለበት ስለሚያሳይ ነው።

ከዚህ ሌላ፣ *ማን ይናገር የነበረ... የታኅሣሡ ግርግርና መዘዙ* አያሌ ከዚህ በፊት የማይታወቁ ኩነቶችን አቅርቦልናል። አፄ ኃይለሥላሴ፣ ኮሎኔል ወርቅነህን ከክብር ዘበኛ መኮንንነት አንስተው የልዩ ካቢኔያቸው የደህንነት ሹም ያደረጉት በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. ነበር። ከዚህ ወቅት እስከ መፈንቅለ መንግሥቱ ድረስ ያለው ጊዜ አጭር ቢሆንም፤ ወርቅነህ ብዙ ጉዳዮችን ያከናወነበት ወይም ቢያንስ ለውይይት ያነሣበት ነበር ማለት ይቻላል። የመሬት ይዞታ ነገር በአእምሮው ውስጥ ይጉላላ እንደነበርና የሪፎርም አስፈላጊነትን አምኖበት እንደነበር ከብርሃኑ ትረካ በግልጽ ማየት ይቻላል (የዚህን መጽሐፍ ምዕራፍ ፲ ይመለከቷል)። ሰውየው ይህንን ታላቅ ጉዳይ አንስቶ መጨነቁ እውነትም ዘመነኞቹ ይሉ

3 Tekeste Melake, "The 1960 Coup d' Etat in Ethiopia," ( MA Thesis Presented to the School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1960), p. 101

እንደነበረው ታላቅ አእምሮ ያለው ሰው እንደነበር ያሳያል። ይሁን እንጂ፣ መፈንቅለ መንግሥቱ ባለመሳካቱ፣ የሐሳብ ጅማሮው አየር ላይ ቀርቷል።

ከግሪንፊልድ ጀምሮ እስከ አሁን የወጡት ጽሑፎች ሁሉ የሚስማሙበት ጉዳይ ብርጋድየር ጀኔራል መንግሥቱ መፈንቅለ መንግሥቱን ማክሰኞ ከሰዓት በኋላ ለመጀመር ከወንድሙ ጋር ሲወስን፣ ኮሎኔል ወርቅነህን እንዳላማከረው ነው። ይህንን ሀቅ አቶ ብርሃኑም ያጠናክራሉ፤ ይሁን እንጂ፣ ከዚህ በፊት በነበሩበት ጊዜያት ሦስቱም የመፈንቅለ መንግሥትን አስፈላጊነት ተወያይተውበት እንደነበረና ተስማምተውበት እንደነበረም መገመት ብቻ ሳይሆን፣ ባለው ማስረጃ መሠረት፣ እንደሀቅም መቀበል ይቻላል። በዚያች ቀንና በዚያች ሰዓት መደረጉን ባያውቅና እርሱም ድንገት የመያዝ ያህል በሆነ ሁኔታ ጉዳዩን ቢረዳውም፤ ኮሎኔሉ ሳያወላውል ነገሩ ውስጥ ይገባበታል። እዚህ ላይ ነው የአቶ ብርሃኑ ትውስታ አዳዲስ ነገሮችን የሚያመጣልን። በመንግሥቱና በወርቅነህ መካከል ታክቲክን አስመልክቶ የሚደረገው ክርክር ሒደቱን ለመረዳት፣ የሁለቱን ሰዎች ባህርይና ምንነት ለመገንዘብ፣ የመፈንቅለ መንግሥቱን መክሸፍም ለመግለጽ እጅግ የሚረዳ ነው፤ የእሥራኤል እና የአሜሪካ ኤምባሲዎች ዲፕሎማቶች ስለወርቅነህ የሚሰጡትም አስተያየት ምን ያህል ፈረንጆቹ ሁኔታውን እንደተረዱት የሚያሳይ ይሆናል።

ይህ ሁሉ እጅግ ጠቃሚ ቢሆንም ከሁሉ ልቆ የሚወጣው ግን መንግሥቱና ወርቅነህ ያደረጓቸው ክርክሮች ናቸው። የወርቅነህ ሐሳብ በአስቸኳይ አንድ መቶ ኃይል ወደ አራተኛው ክፍለ ጦር ኮማንድ ፖስት (መሿለኪያ አጠገብ) ሔዶ፣ እዚያ ያሉትን ጄኔራሎች ቢቻል መያዝ፣ ካልተቻለ መደምሰስ አለበት የሚል ነበር፤ ይህንን የኮማንዶ ኦፕሬሽንም ካስፈለገ ራሱ ለመምራት ዝግጁ እንደሆነም ገልጾ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ጄኔራሉ በማያወላዳ ምክንያት፣ አልተቀበለውም፤ ጉዳዩም በዚህ ተዘጋ። ይህ አለመግባባት ወርቅነህ ጉብዝ፣ ፈጣንና ብሩህ አእምሮ የነበረው ሰው እንደነበረ ፍንትው አድርጎ ያሳያል። ስለእርሱ ተክለሰውነትና ችሎታ ዘመነኞቹ ይሉት የነበረውን ሁሉ የሚደግፍ ይሆናል፤ እውነትም፣ ወርቅነህ ቀላል ሰው አልነበረም፤ እውነትም፣ አፄ ኃይለሥላሴ ሰው መምረጥ ያውቃሉ የሚያሰኝ ነው።

የአቶ ብርሃኑ ትረካ ብዙ ነገር አካቷል። ስለወርቅነህ አሟሟት የመጀመሪያው ገለጻ የቀረበው በግሪንፊልድ ነበር።[4] ከዚያ ወዲህም፣ አንዳንዶቹ መጻሕፍት አጠር አጠር አድርገው አቅርበውታል፤ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ግን ለወርቅነህ እጅግ በጣም ታማኝ ስለነበሩ (ይህም በጣም የሚያስደንቀው ባህርያቸው ነው!)፣ አለቃቸው የትና እንዴት

[4] Greenfield, p. 434

እንደወደቀ *ሥራዬ* ብለው ተከታትለው ለማጣራት ሞክረዋል። ገለጻቸው፣ ሌሎቹ ባጭሩ ያቀረቡትን ምስክርነት አስፋፍቶ ያቀርባል፤ የተሻለ ተአማኒነትም አለው። ስለዚህ፣ ስለክሎኔሉ አሟሟት ከአሁን በሁዋላ እርግጠኛ ሆኖ መጻፍም ሆነ ማውራት ይቻላል።

*ማን ይናገር የነበረ... የታኅሣሡ ግርግርና መዘዙ* በነዚህ እላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ብቻ ሳይሆን፣ በሌሎችም ጉዳዮች እንዲሁ አስተዋጽኦ የሚያደርግ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ታላቅ ትውስታ ነው። ለዚህም ብዙ ዝርዝር ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። የራሳቸው የአቶ ብርሃኑ የሕይወት ጉዞም ለማህበራዊ ታሪክ ጥናት ጠቀሜታ አለው። እስካሁን እያሌ የዘመኑ ምሑራን የሕይወት ታሪካቸውን አቅርበዋል፤ *ማን ይናገር የነበረ... የታኅሣሡ ግርግርና መዘዙ* አንድ ተጨማሪ አስተዋጽኦ ይሆናል። ይህ መጽሐፍ ሀገራችን ኢትዮጵያ ሀ ብላ ለውጥ ከመጀመሯ በልሂቃኖቿ መካከል ስለተነሱት የሐሳብ ልዩነቶች የሚያስረዳ ጥሩ መረጃ ነው።

ባጭሩ፣ ይህ *ሥራ* የ፳ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያን የፖለቲካና የማህበራዊ ታሪክ የሚያጠኑ ተመራማሪዎች በእጅጉ ሊጠቀሙበት የሚችሉት መጽሐፍ ነው።

ሽፈራው በቀለ
የኢትዮጵያ ታሪክ ፕሮፌሰር
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# መግቢያ

እስከአሁን ስለመፈንቅለ መንግሥቱ ከተጻፉት መጻሕፍት *ፋና ወጊ* በይሆን ዓለም ሰገድ ነሐሴ ፲፱፻፹፬ ዓ.ም.፣ *የሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ልእለ ሥራና የ፲፱፻፶፫ቱ ዓ.ም. መፈንቅለ መንግሥት ትክክለኛ ገጽታ* በይላቅ ኃይለማርያም ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. እና *የ፲፱፻፶፫ቱ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራና ከ፲፱፻፳ - ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የኢትዮጵያ ታሪክና ፖለቲካዊ ሂደት* በኮሎኔል ቃለ ክርስቶስ ዐባይ የሚጠቀሱ ናቸው። እንዲሁም በተለያዩ መጽሔቶችና ጋዜጦች ስለመፈንቅለ መንግሥቱ የተለያዩ ገጽታዎች እንደየአዘጋጆቹ አመለካከትና አቀራረብ ብዙ ተጽፏል። እነዚህን ሥራዎች አስመልክቶ ጸሐፊው ጉዳዩን ከየት አገኘው? ቀረቤታውስ እስከምን ነበር? ... ወዘተ. የሚሉ ጥያቄዎችን ማስነሣቱ አይቀርም። ይህም መጽሐፍ ሲዘጋጅ በተመሳሳይ ርእስ ጉዳይ ቢቀርብም፤ ብዙ የራሱ አዲስ ዓይነተኛ አስተዋፅኦና መረጃው ከተገኘበት ተፈጥሮ አንጻር ልዩ ዋጋ እንደሚኖረው ታምኖበት ነው።

መጽሐፉ ሦስት ክፍሎች ሲኖሩት፤ የመጀመሪያው የ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. መፈንቅለ መንግሥት ለምን ተነሣ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ይሞክራል። ሁለተኛው ክፍል በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ እንቅስቃሴ ዋና ዋና ተዋናዮችና የሙከራው ሂደት ምን እንደሚመስልና ለምን እንደ ወደቀ ይተርካል። ሦስተኛው ክፍል የመፈንቅለ መንግሥቱን ውጤትና ትቶት የሔደውን አሻራ ያመለክታል።

ስለመፈንቅለ መንግሥቱ ለመጻፍ ምክንያት የሆነኝ በሒደቱ የመሳተፍ ዕድል በማግኘቴ ነው። ስለዚህ ለዚህ ዕድል ያበቃኝን የታሪክ አጋጣሚ ለማውሳት የልጅነት ዕድገቴን ወደትምህርትና የሥራ ሕይወቴ የገባሁባቸውን አጋጠሚዎች በማካተት በምዕራፍ አንድ ላይ ቀርቧል።

ምዕራፍ ሁለት ለ፲፱፻፶፫ቱ ዓ.ም. መፈንቅለ መንግሥት መነሻ የሆኑ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማኅበራዊ ችግሮችን ስረ መሠረት ወደኋላ በመሔድ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አመሠራረትን በመዳሰስ ለማሳየት ይሞክራል። መፈንቅለ መንግሥቱ የተካሔደው በወታደራዊው ክፍል ስለሆነ፤ ለማክሸፍም የተሰለፈው ወታደራዊው ክፍል ስለሆነ የክብር ዘበኛና የጦር ሠራዊት ሁለት ወደረኞችን አቋቋምና የቅራኔያቸው ሒደት የመጨረሻው ደረጃ የደረሰበትን ምክንያት ለመገንዘብ እንዲያስችል የዚሁ ምዕራፍ አካል ተደርጓል።

በሦስተኛው ምዕራፍ የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎችና ተዋንያን በመሬት ስሪት፣ በፍርድ አሰጣጥ፣ የንግግርና የጽሑፍ ነጻነት አለመኖር፣ ተገቢውን ሠራተኛ በተገቢው ቦታ አለማዋልን በዚህም የተነሣ ብሶቱ በሁሉም አቅጣጫ ሲጠራቀም ሕዝብ መሸከም ከሚችለው በላይ እየሆነ መምጣቱን ስለመገንዘባቸው

የሚያመለክተውን መረጃ ለማካተት ጥረት ተደርጓል። የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ንጉሠ ነገሥቱ ሳይነኩ አስተዳደሩን ቀስ በቀስ በማሻሻል ወደ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲለወጥ፣ የንጉሡ ብቸኛ ሥልጣን መግቻ እንዲኖረውና በመንግሥቱ የሥልጣን ድልድል ላይ ያሉ ኃላፊዎች ደግሞ ለሚያደርጉት ጥፋት ተጠያቂነት እንዲኖርባቸው የነበራቸውን ፍላጎትና ያደረጉትን ጥረት መዝግቧል። ስለዚህ መፈንቅለ መንግሥቱን ብዙ ሰዎች እንደሚገምቱት እንደብልጭታ በቅጽበት የተከሰተ ዱብዕዳ እንዳልሆነ ለማሳየት ተሞክሯል።

ይህንንም እነዚህ በርከት ያሉ አገራቸውንና ወገናቸውን የሚወዱ፣ የችግሩ ብዛትና ክብደት ያንገበግባቸው የነበሩ ምርጥ የክብር ዘብኛ መኮንኖች አስተዳደሩ የነበረውን ችግር በቅጡ አጥንተው በደረሱበት ድምዳሜ ምክንያት የመንግሥት ሥርዓቱ ለውጥ እንደሚያስፈልገው በማመናቸው እንቅስቃሴ በማውጠንጠን ላይ ሳሉ፤ ንጉሡ ለጄኔራል መንግሥቱ ወንድማቸው ገርማሜ ንዋይ ወደጅጅጋ እንዲሔድ እንዲያደርጉ ባዘዙበት ቴሌግራም አስገዳጅ ሁኔታ የገቡበት መሆኑንና ይህም ለውድቀቱ ምክንያት ሊሆን እንደቻለ፤ የቃልና የሰነድ መረጃዎቹን እንደወረዱ በማቅረብ ለማሳየት ተሞክሯል። በዚህ መሠረት ምዕራፍ አራት፣ አምስት፣ ስድስት እና ሰባት መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ሊኖር እንደሚችል የወጡ ፍንጮች (ጠቋሚ ሁኔታዎች)፣ የመፈንቅለ መንግሥቱ እንቅስቃሴ አይቀሬ ሆኖ ወደድርጊት ሲገባ በሁለቱ ተፋላሚ ኃይሎች መካከል የተደረጉ ዝግጅቶች፣ የመፈንቅለ መንግሥቱ እንቅስቃሴ አፈጻጸምን በጊዜና በቦታ እየለዩ አቅርበዋል። በእነዚህ ምዕራፎች መፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶባቸው በነበረበት ሦስት ቀናት (ታኅሣሥ ፯-ታኅሣሥ ፱) በአንድ በኩል በተፋላሚዎቹ ሁለት ኃይሎች በሌላ በኩል ለጉብኝት ውጪ ሃገር በነበሩት ንጉሡ ዙሪያ በተመሳሳይ ሰዓት የተከወኑ ጉዳዮችን አንባቢው የጊዜ ቅደም ተከተላቸው ሳይፋለስበት በቀላሉ እንዲረዳ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጎበታል።

መፈንቅለ መንግሥቱ ትቶት ስለሔደው አሻራ በታተተበት በምዕራፍ ስምንት ስለመፈንቅለ መንግሥቱ ተሳታፊዎች የፍርድ ሒደት የራሴን የፍርድ ሒደት እንደማሳያ በመጠቀም ቀርቧል። በተለይ መፈንቅለ መንግሥቱን ተቃውመው ያከሸፉት የዘውድ ደጋፊዎች ሳይቀሩ ዘግይቶም ቢሆን መፈንቅለ መንግሥቱ ተገቢ ምክንያት እንደነበረው ማሰብ ስለመጀመራቸው እንድያውም በእግዚአብሔር ቸርነትና በንጉሡ እድልና ብርታት ብቻ እንደከሸፈ መደምደሚያ ላይ በመድረሳቸው ሊወሰድ ይገባቸዋል ያሉዋቸውን ማሻሻያዎች በማስታወሻ መልክ ማቅረባቸውን በሰነድ አስደግፌ አቅርቤአለሁ። ከእነርሱ ውስጥ ማስታወሻዎቹ ረቂቅም የሆኑትን

ድርሟቸውን በመጽሐፉ ዝርዝር አድርጌ ዋናዎቹን ሰነድ በአባሪነት ከመጽሐፉ መጨረሻ ተያይዟል። በግል የደረስኩባቸውና በ፲፱፻፷ዎቹ መጀመሪያ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አሳሳቢ ሁኔታ ላይ መሆኑ ግምት ተወስዶ የጥንቃቄ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስቡ ቡድኖች ያደርጓቸው የነበሩ እንቅስቃሴዎች እንደነበሩ ተጠቁሟል።

በመጨረሻም ምዕራፍ ዘጠኝ አገሪቱ በነበረችበት የፖለቲካ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ምክንያት በግል ሕይወቴ ያለፍኩባቸው የሕይወት ገጠመኞችን ይዟል። በዚህ ምዕራፍ በመፈንቅለ መንግሥቱ ሳቢያ ከእሥር ከወጣሁ በኋላ በግዞት እንድቀመጥና ሥራ እንዳላገኝ ስለተደረገው ሙከራ፣ በመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ተሳትፈው ከእሥር የተፈቱ ሰዎችን ከአዲስ አበባ ለማራቅ ሲወሰን በኦጋዴን ልማት ሥራ አስኪያጅነት በመመደቤ ያደረግሁትን አስተዋፅኦና በጎንደር ስላካሔድነው የልማት እንቅስቃሴና ሰላም የማስፈን አስተዋፅኦዬ፣ ቀርቦበታል።

ባጠቃላይ መጽሐፉ ለሁለት ዓይነት አንባቢዎች እንደሚጠቅም ተስፋ አለኝ። አንደኛው ስለንጉሡ ዘመን የመንግሥት የፖለቲካና ኢኮኖሚ አስተዳደር ለሚያጠኑ የታሪክ፣ የሕግና የፖለቲካ ባለሙያዎች ነው። አጠቃላይ ሕብረተሰቡም የዘመኑን አስተዳደር አሁን ከተደረሰበት የመንግሥት አስተዳደር ዘይቤ አንጻር ለማነጻጸር እንደሚረዳው ይታሰባል። ሁለተኛው በመፈንቅለ መንግሥቱ ሒደት የተካፈሉና የሰሙ ባጠቃላይ በወቅቱ ለነበሩት ሁሉ ትዝታቸው እንዲሆን ነው። ለዚህ ሠፊ ዐላማ እንዲረዳም የመረጃዎች ምንጭና ሌሎች ማብራሪያዎች በግርጌ ማስታወሻ እንዲገለጹ ተደርጓል።

የመጽሐፉ የመጀመሪያና የመጨረሻ ምዕራፎችም በግል የእኔን ሕይወት የሚዳስሱ ናቸው። ይህም በዚህ መጽሐፍ የቀረበውን የመፈንቅለ መንግሥቱን ሙከራ ታሪክ ተራኪ ማንነት፣ አስተዳደግና ዕጣ ፈንታን ለማሳየት እንዲረዳ ብቻ ሳይሆን፤ በሚተረከው ሁነት ላይ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ያደረገውን የእኔን ማንነትም እንዲያሳይ ነው። መቼም ባደግንበት ባህልና በግል ተፈጥሮአችን ስለራሳችን መናገርም ሆነ መጻፍ ይከብደናል። ምክንያቱ ያለውን እንዳለ ቢጻፍ ምንም ይሁን ምን እንዴት አድርጎ ራሱን አጋነነ ወይም ግብዝ ሆነ ያሰኛል። እራሱን ዝቅ አድርጎ ቢጽፍ ደግሞ ይህ ምን ፍሬ ነገር አለው ብሎ ነው ታዲያ የሚያቀርበው ተብሎ ይነቀፋል። እንግዲህ እኔም ይህ ሁሉ እየተሰማኝ ነው ሙሉውን እንኳን ባይሆን ከፊሉን በተቻለ መጠን በእውነት ለማቅረብ የሞከርኩት። የመፈንቅለ መንግስቱ ታሪክ ከእኔ ታሪክ ጋር በአንድ ላይ ሲቀርብም አንባቢውን እንዳያስቸግር እኔን አስመልክቶ ያለው ትረካ

በመጀመሪያና በመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች ተቀምጧል። ምዕራፍ ስምንት ላይ በመፈንቅለ መንግሥቱ ተሳታፊነት የተከሰሱ ሰዎች የክስ ሒደትን የሚመለከተው ክፍል ላይ የኔ ክስ ሒደትና ምልልስ ሽፋን ከማግኘቱ በስተቀር፣ ከላይ ከጠቀስኳቸው ሁለት ምዕራፎች ውጭ በሌሎቹ ምዕራፎች የእኔ ሥራ የተካተተው እንደማንኛውም የመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ተሳታፊ ብቻ ነው።

ይህን ካልኩ፣ ከመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ በፊት የወላጆቼና የልጅነት አስተዳደጌ መካተቱ፣ አሁን ወደኋላ ሳስበው ከአባቴ ወሳኝነትን፣ ድፍረትና ፍጥነትን፣ ከእናቴ ርህራኄን፣ ከአያቴ ከእሜቴ ዓለሜ ማስተዋልን የወረስኩ መሆኑንና የእኔን ባህሪ በእጅጉ የቃኙ ስለሆኑ ተገቢነቱ አከራካሪ ስላልሆነ ነው። ልክ እንዲሁ ከመፈንቅለ መንግሥቱ ወዲህ ያለው ታሪኬ መካተቱም በአንድ በኩል በመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ሳቢያ ያጋጠመኝን ያመለክታል። በሌላ በኩል ደግሞ ከመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ መሪዎች አለቆቼ ጋር በመሥራቴ የወረስኩትን ለአገርና ለወገን አሳቢነትና ለሕዝብ የተቆርቋሪነት መንፈስ ለማሳየት ነው።

ምንም እንኳን አንባቢ በውስጥ ዝርዝሩ የሚያገኘው ቢሆንም ይህን መጽሐፍ የጻፍኩበትን ሁኔታ ከወዲሁ ጥቂት ሳልል ማለፍ ተገቢ አይሆንም። በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. መፈንቅለ መንግሥቱ ሲጠነሰስ እኔ ፈልጌና አስቤ በእንቅስቃሴው ውስጥ የተደራጀሁ ሳይሆን ወደእንቅስቃሴው የገባሁት በድንገት ነበር። ይህም ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ጋር በደንብ ለመተዋወቅ ባገኘሁት አጋጣሚ የሚጀምር ክስተት ነው። አንዴ ከገባሁ በኋላ ግን ከመንፈሱ ለመውጣት የወቅቱ የሞራልና የፖለቲካው እምነት የሚፈቅድልኝ አልነበረም። ለዐላማው መሣካት ከ፲፱፻፶፪ እስከ ታኅሣስ ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ድረስ አቅም በፈቀደው ሁሉ በመፈንቅለ መንግሥቱ በመተባበር ዘልቄአለሁ። በመጨረሻም በመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ሳቢያ በወህኒ ቤት ለእሥር ተዳርጌአለሁ።

የዚህ መጽሐፍ ጅማሬ የተወጠነው በ፲፱፻፶፬ ዓ.ም. ወህኒ ቤት በነበርኩበት ጊዜ እዚያ አብረውኝ ከታሠሩ የክብር ዘበኛ አባላት ስለመፈንቅለ መንግሥቱ የማያውቁትን ሁሉ እንዲገልጹልኝ በመጠየቅ ነው። በእሥር ቤቱ በፍርድ የተገደሉትንም ጨምሮ ከሚገኙት ብዙዎቹንም በመጠየቅ በቃል የገለጹልኝን በመያዝ እንደ ውዳሴ ማርያም ስደጋግም ለሰዎችም ሳጫውት ከኖርኩ በኋላ፣ ፍርዱ ከስምንት ወደአምስት ዓመት በይግባኝ ተቀንሶልኝ አምስት ዓመት ታሥሬ በ፲፱፻፶፰ዓ.ም. በታኅሣሥ ወር ስፈታ፣ አንዳንድ መንደርደሪያ ሐሳቦችን ብቻ በወረቀት ማስፈር ጀመርኩ። በዚህ መካከል በ፲፱፻፷ዓ.ም. የዐፄ ቴዎድሮስን ፻ኛ የሙት ዓመት ለማክበር ኢትዮጵያውያንን ይዤ ወደ መቅደላ ሔጄ ስመለስ፣ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ‹‹፻ኛ ሙት ዓመት›› በሚል ርእስ ስለጉብኝቱ በመውጣቱ በጊዜው በነበሩ የመንግሥት

ተቆርቋሪዎች ነን ባዮች ከዐፄ ቴዎድሮስ በኋላ የነበሩትን መቶ ዓመታት ሙት ናቸው ለማለት እንደታሰበ አስቶጥሮ የጥፋት መልዕክተኞች ቤቴን በርብረው ሰነድ መያዣ ቦርሣዬን ከአያሌ ማስታወሻዎችና ሰነዶች ጋር በመውሰዳቸው ጽሑፉን ለብዙ ዓመታት ማቋረጥ ግድ ሆኖብኝ ቆየሁ። እንደገና በተለያዩ ቦታዎች የተቀመጡ ማስታወሻዎቼን በመጠቀም ስለመፈንቅለ መንግሥቱ የማውቀውንና ከሌሎች ያሰባሰብኩትን መረጃ በማቀነባበር ማዘጋጀት ብጀምርም የዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ወርዶ ወደ ሥልጣን በመጣው የደርግ ዘመንም በተለያዩ ምክንያቶች ቤቱ መፈተሹ እንደማይቀር ስለገመትኩ ማንም ቢመጣ ዘፈን መስሎት ትቶት እንዲሔድ በማሰብ ሥራውን በቴፕ ቀድቼ ከዘፈን ክሮች ጋር አቀላቅዬ አስቀመጥኩት። እንዳጋጣሚ ግን ይሔንንም ሌባ ሌሊት ገብቶ የነበሩትን የሙዚቃ መሣሪያዎች በሙሉ ሲወስድ ታሪኩን የቀዳሁባቸውን የቴፕ ክሮችም ዘፈን መስለውት ስለወሰዳቸው እንደገና ከሥር ታሪኩን ለመዘገብ አስገድዶኛል።

ይሁን እንጂ አሁንም በተለያየ ጊዜ የተያዙ ማስታወሻዎቼንና ትውስታዎቼን ሰነዶችን ከያሉበት በማሰባሰብና የቃል መረጃዎችንም ለማጠናቀር እንደገና ባደረግኩት ጥረት ለዚህ መጽሐፍ ዕውን መሆን ያስቻለኝን የመጀመሪያውን ረቂቅ ለማዘጋጀት ቻልኩ። ከዚህ በኋላ በወቅቱ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ዳይሬክተር ለነበሩት ለፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መጥቼ በቃል ስለሥራው ሳነጋግራቸው፤ የታሪኩን ፍሬ ነገር አጠር አጠር እያደረግሁ ለሁለት ሰዓት ያህል ገለጽኩላቸው። እሳቸውም አቀራረብህ እንደወረደ በመሆኑ በጽሑፉም ልክ እንዲሁ መሆን እንዳለበት ከመከሩኝ በኋላ ለጉዳዩ ቅርበት ያለው ያን ጊዜ ዶክተር (ኋላ ፕሮፌሰር) ባህሩ ቢመለከተው ጥሩ ይሆናል ስላሉኝ፤ በተመሳሳይ ለፕሮፌሰር ባህሩ አስረዳሁ። ፕሮፌሰር ባህሩም ርዕስ ጉዳዩ ጥሩ መሆኑን ከገለጸልኝ በኋላ ብዙ የሚታረሙ ነገሮችም ስላሉበት ጊዜ ሳይወስድ በፍጥነት እንዲታተምም እርሱም አስተካክሎት በጋራ እንድናወጣው ሐሳብ አቀረበልኝ። እኔ ግን የወሰደውን ጊዜ ያህል ወስጄ አስተካክዬ ማውጣትን ስለመረጥሁ የተወሰነ ጊዜ መቆየት ግድ ሆነብኝ።

ከዚህ በኋላ የእርትኦት ሥራ እንዲሠራልኝና አንዳንድ ምክር ለማግኘት ሰው ሳፈላልግ አቶ አስፋው ዳምጤን አግኝቼ ረቂቁን ሰጥቼ ስለክፍያው እንነጋገር አልኩት። እርሱም መጀመሪያ ረቂቁን የምቀበለው ስለመሆኑና አለመሆኑ ማየት አለብኝ ብሎ ሰጠኹት። በሚቀጥለው ጊዜ ስንገናኝ ረቂቁን እንዳደነቀውና አንተ ለአገር ብለህ ስትሠራ እኔ የማልረዳበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ለዚህ ደግሞ ክፍያ አልጠይቅም ብሎ ከወሰደ በኋላ ለፕሮፌሰር ሺፈራው በቀለ ስላሳየው የማያውቀኝ ፕሮፌሰር በረቂቁ ላይ ቢስተካከል ያለውን የመረጃ አቀራረብ ጉዳይ በጽሑፍ፣

ግምገማውን ማለፍ ከቻለ ኅትመቱም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ቢሆን እንደሚሻል በቃል ስለመከረኝ፤ ረቂቁ በሙያተኞች ደረጃ ዋጋ ያለው መሆኑን እንዳምን ረድቶኝ ለዝግጅቱ መጠናቀቅ ጉጉትም ትጋትም እንዲያድርብኝ አደረገ።

የፕሮፌሰር ሺፈራው ምክር ረቂቁ መታተም የሚገባው መሆኑን፣ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ያለውን የታሪክ ክፍተት የሚሸፍን ስለሆነ፤ በረቂቁ የተካተቱትን ሰነዶች አንባቢም ሆነ ተመራማሪ ፈራ ተባ ሳይል ለመጠቀም እንዲችል እንዴትና ከየት እንዳገኘኋቸው መግለጽና ለታሪኩ እንዴት ቅርበት እንዳበጀሁ ሊያሳይ የሚያስችለውን የራሴን የሕይወት ታሪክ መካተት እንደሚገባው፣ ረቂቁም ከኅትመት በፊት ከፍተኛ አርትኦት ሊሠራበት እንደሚገባ የሚያመለክት ነበር። የፕ/ር ሺፈራው ምክር እውነትም መጽሐፉ የዛሬውን መልክ እንዲይዝ ለማድረግ እንደገና እንድጽፈው በእጅጉ ረድቶኛል። ከዚህ ውስጥም

> ይኽንን መጽሐፍ ሲጽፉ ስለራስዎ ያልጻፉት ምናልባት ታሪኩ የኔ አይደለም፣ ስለራሴ ባወራ ታሪኩ ላይ ያጠላበታል ከሚል አስተሳሰብ ተነስተው ሊሆን ይችላል፤ ይህ ከሆነ ምክንያቱ የማደንቀውና የማከብረው ፈረንጆች noble የሚሉት አስተሳሰብ ነው። ነገር ግን የርስዎን ማንነት፣ ከባለጉዳዮቹና ከሰነዶቹ ጋር ያለዎትን ቅርበት ማወቅ ለመጽሐፉ ምስክርነት ተአማኒነት ስለሚሰጠው፤ ታሪኩን ሳያጠላበት፣ ስለራስዎም በየቦታው ቢናገሩ ጥሩ ይመስለኛል።

የሚለው አስተያየት አንዱ ነበር። እኔም በዚህ መሠረት በረቂቁ ላይ የተቻለኝን ጥረት አድርጌበት ከብዙ ልፋት በኋላ ጥቅምት ፪ሺ፱ ዓ.ም. ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ ለማስረከብ በቃሁ። ዩኒቨርስቲ ፕሬሱም ተገቢውን ግምገማ በባለሙያዎች አስደርጎ ረቂቁን ለኅትመት ለማብቃት የሚያስፈልገውን መሻሻል ለማሟላት ከእኔ ጋር የሚሠራ አርታኢ ስለመደበ፤ ሰፊ ጊዜ ወስደን መጽሐፉ አሁን ያለውን አወቃቀር፣ የምንጭ አጠቃቀምና አገላለጽ እንዲኖረው ለማድረግ ተችሏል። በዚህ አጋጣሚም ጊዜ ወስዶ ሁሉን ችሎና ታግሦ ጽሑፉ ተገቢውን የመጽሐፍ ቅርፅ ይዞ እንዲወጣ ከግምት በላይ አስተዋፅኦ ያደረገውን አቶ ብርሃኑ ደቦጭን አመሰግናለሁ።

መጽሐፉ በተለይ በግል በመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ላይ ከጥንስሱ እስከ ፍፃሜው አብሬ የነበርኩ በመሆኑ የመፈንቅለ መንግሥቱ ሞካሪዎች በመሬት ሥሪትና ይዞታ ግብር ላይ ባስደረጉት ጥናት ድርሻዬን እንድወጣ በተሰጠኝ ኃላፊነት የተረዳኋቸውን ብርቱ ምስጢሮችና ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ጋር በግል በነበረን የሥራ ቅርበት ምክንያት ያወቅኋቸውን ምስጢራዊ ፍንጮች አክዬ ያቀረብኩበት ነው።

በመፈንቅለ መንግሥቱ ውስጥ ተካፍለው ወይም በተለያየ ደረጃ ተነካክተዋል በሚል የታሠሩ፣ መፈንቅለ መንግሥቱን በማክሸፉ የተሳተፉና በተለያየ ደረጃ ስለሁኔታው የሚያውቁ ከሠላሳ ሰዎች በላይ ምንጭ በሆኑበት ጉዳይ አንደኛ ደረጃ ማስረጃ የሚሆኑ ሰዎች በጽሑፍና በቃል የሰጡኝን መረጃ አካትቼአለሁ። በንጉሡና በከፍተኛ ባለሥልጣናት መካከል የተደረጉ ምስጢራዊ የደብዳቤ ልውውጦችን ለማግኘት በመቻሌም ፳ የሚደርሱትን ለመጽሐፉ ከፍተኛ ዋጋ በሰጡበት መልኩ ተጠቅሜባቸዋለሁ። እነዚህን ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው መረጃዎች በከፍተኛ ጥረት ለማግኘትና በዚህ መጽሐፍ ለማቅረብ በመቻሌ፤ መጽሐፉ ለሚታወቀው ጉዳይ ዝርዝር ማስረጃ የሚያቀርብና የሚያብራራ፣ ለማይታወቀው አዲስ መረጃና ዝርዝር የሚሰጥ ለማድረግ ተችሏል።

በእንግሊዝ አገር በፐብሊክ ሪኮርድ ኦፊስ ያሉ ሰነዶችን ለመጠቀም በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. ያደረኩት ሙከራ ግን ሰነዶቹን ለማሰባሰብ በቂ ጊዜ ስላስፈለገና እኔም የተፈለገውን ያህል ጊዜ መቆየት ባለመቻሌ ሊሳካልኝ አልቻለም። ስለመፈንቅለ መንግሥቱ ብዙ መዛግብት አለው በሚባለው በካሊፎርኒያ ዩኒቨርስቲም ሰነዶችን ለማግኘት ያደረኩት ጥረት አልተሳካልኝም። በዚህ መጽሐፍ ከእነዚህ ቦታዎች የሚገኙ መረጃዎችን ለማካተት ባይቻልም፤ ወደፊት በጉዳዩ ላይ ሠፊ ምርምር የሚያደርግ ፍለጋውን ከሚያተኩርባቸው ቦታዎች እንደሚሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ።

መጽሐፉ ለኅትመት ሲደርስ ረቂቁን ለማዘጋጀት ፲፭ የሚደርሱ ጸሐፊዎች የተፈራረቁበትና በተለያየ የኮምፒውተር ፕሮግራምና የፊደል ቅርፅ በተለያየ ጊዜ የጻፉት በመሆኑ በአንዱ ኮምፒውተር የተጻፈው በሌላ አልነበብ እያለ ቃላቱን መልቀሙ አታካች መሆኑ አልቀረም። መጽሐፉ ‹ከአዲስ ዘመን›፣ ‹ከሰንደቅ ዓላማው›፣ ‹ወታደርና ጊዜው›፣ ‹ወታደርና ዐላማው›፣ ‹ፖሊስና እርምጃው› ጋዜጦች ከኢትዮፒያን ኦብዘርቨር›፣ ‹መነን›ና ‹ኢትዮፒያን ሚረር› መጽሔቶችና ከግለሰቦች የተገኙ የታሪኩ አካል የሆኑ ሰዎችን ፎቶዎች አካቶ ይዟል። ይሑን እንጂ በተለይ ከቆዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች የተወሰዱት ፎቶዎች ጥራት ብዙ ቢለፋበትም የሚያረካ ላይሆን ቀርቷል። በተቻለ መጠን ነገሮችን ለማጥራት ቢሞከርም የአንዳንድ ስማቸው የተጠቀሱ ሰዎችን የአባት ስም ለማግኘት ባለመቻልና ወቅታዊ ወይም የኋላ የማዕረግ ስም ያልተጠቀሰላቸው ሊኖሩ እንደሚችሉ የንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ባለቤት ወይዘሮ የሺመቤት መባል ሲገባቸው በእንጥልጥል የሺመቤት መባላቸውን መጥቀስ ይቻላል።

በተረፈ ይህ መጽሐፍ ለአንባቢ ሲደርስ በእኔ ደረጃ የሚታወቀውን ብቻ ላይሆን በመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ በአካል የተሳተፉና በተለያዩ ምክንያቶች ስለ መፈንቅለ መንግሥቱ ለማወቅ ዕድሉ የነበራቸው ኢትዮጵያውያንን መረጃ ያካተተ

መጽሐፍ ስለሚሆን ጉልህ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ አምናለሁ። የመፈንቅለ መንግሥቱ ታሪክ በዚህ መጽሐፍ ተካቶ አልቋል ለማለት ግን አልደፍርም። ስለመፈንቅለ መንግሥቱ ጥንስስ ሒደት ገና ያልተደረሰባቸው ምስጢሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ አስባለሁ። ምክንያቱም የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ምስጢሩ እንዳይወጣ ለጥንቃቄ ሲባል የሥራው ተካፋይ የሚሆን ሰው ሲያነጋግሩ፣ በአገሪቱ ላይ እየደረሰ ስላለው በደልና ችግር እየነገሩ ቁጭት እንዲሰማው በማድረግ የሰውየውን አቀባበል በመገምገም ፍንጭ ብቻ እየሰጡ የቀረውን አንተ ድረስበት የማለት ዘዴ ይጠቀሙ ስለነበር ነው። በግል መፈንቅለ መንግሥት ልናደርግ አስበናል ትተባበራለህ ወይ ብለው የጠየቁት ከሌ/ጄኔራል ኀጋ ኃይለ ሥላሴ በቀር ሌላ ሰው እስካሁን አላጋጠመኝም። ለማንኛውም እኔ የደረስኩበትን ያህል እነሆ ብያለሁ።

# ክፍል ፮

# የታኅሣሡ ግርግር ለምን ተነሳ?

# ምዕራፍ ፩

# የታሪኬ አጋጣሚ[1]

የተወለድኩት ንጉሥ ተፈሪ ለንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣን በበቁበት በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም. ነው። እናቴ በልጅነቴ እንደነገረችኝ፣ እናቴና አባቴ የተጋቡት በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም. ቢሆንም፣ እስከ ፲፱፻፳፩ ዓ.ም. መጋቢት ወር ድረስ እናቴ ከአባቴ ልጅ አልወለደችም ነበር። በዚያን ጊዜ ሴት ልጅ ባገባች በዓመቱ ቢዘገይ በሁለተኛው ዓመት ልጅ መውለድ የነበረና የሚጠበቅ ነበር። በወቅቱ ልጅ ትልቅ ሀብት፣ ክብር፣ ፀጋና ኩራት ነበርና፣ በዓመቱ ወይም በሁለተኛው ዓመት ካልወለደች መከነች ተብሎ ወዳጅ ዘመድ ሁሉ በጐሪጥ የሚያያት ትሆናለች። እናቴም የዚሁ ትችት ሰለባ መሆኗ አልቀረም። የአባቴ እናት እሜቴ ዓለሜ ከቤታቸው ተነሥተው አንድ ኪሎ ሜትር በማይሞላ ርቀት ላይ ወደምትገኘው ወደ አድስጌ ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን (በስሜን አውራጃ ) በበቅሎ ሲጓዙ፣ ከተለመደው አጀብ በተጨማሪ እናቴን ጨምሮ በስድስቱ ወንድ ልጆቻቸው ሚስቶች፣ በበቅሎዎቻቸው ግራና ቀኝ ይታጀቡ ነበር። በእንዲህ ዓይነት አጀብ ሲሔዱ፣ ከእኔ እናት በቀር፣ ሁሉንም ምራቶቻቸውን ያነጋግራሉ። እናቴ አንድ ቀን ትከፋና ‹‹እሜቴ፣ እኔስ የልጅዎ ሚስት አይደለሁም ወይ? ሌሎቹን ሁልጊዜ ሲያነጋግሩ እኔን የማያነጋግሩኝ ምን አጥፍቼ ነው?›› ብላ ብትጠይቃቸው፣ እሳቸውም ‹‹ሌሎቹማ ዓይኔን በዓይኔ አሳይተውኛል። አንቺ ምን አድርገሽልኛል? መልክ ዓይቶ፣ ቁመና ዓይቶ፣ በቅሎ አግብቶ›› ብለው እንደመለሱላት ታስታውሳለች። አባቴ ዘመቻ መሔዱም ላለመውለዷ አንዱ ምክንያት ሳይሆን አልቀረም። አባቴ የደጃዝማች አያሌው ብሩ አጋፋሪ ስለነበር፣ እሳቸው "አንችም" ቋና[2] ሲዘምቱ ነው አብሮ የዘመተው። ደጃዝማች አያሌው ብሩና ራስ ጉግሣ ወሌ የቅርብ ዘመዳማቾች ሲሆኑ፣

---


1 *አንባቢ የዚህ ታሪክ ጸሐፊ ማነው? ከየት? እንዴት ? ከምን? ተነስቶ ይሆን ሲል ጻፈ ማለቱ ስለማይቀር ፤ ለታሪኩ አጋጣሚ የፈጠረውን ስለልደቴ፣ እድገቴ፣ ትምህርቴና ሥራዬ በአጭሩ የማቀርብበት ነው።*

2 *ለቋና "አንቺም" ጦርነት ምክንያት የሆነው ንጉሥ ተፈሪ የንግሥት ዘውዲቱን አልጋ ገልብጠው ዘውዱን ለመውረስ እየተንቀሳቀሱ ነው የሚል ወሬ በአዲስ አበባ በመናፈሉ ነው። ይህንን ሁኔታ ለመግታትም የግቢ ዘበኞች አዛዥ ደጃዝማች አባውቃው የተቃውሞ እንቅስቃሴ አድርገው ነበር። በተመሳሳይ አድማውን በአጭር ለመቅጨት የተነሱት የንግሥት ዘውዲቱ ባለቤት ራስ ጉግሣ ወሌ ነበሩ። ራስ ጉግሣ ወሌ ይህን አድማ ለማክሸፍ የሚችል ኃይል ለማደራጀትና ለማጠናከር ለእንደራሴው ለንጉሥ ተፈሪ ሳያሳውቁና ሳያስፈቅዱ ከአዲስ አበባ ወጥተው ወደ ግዛት አገራቸው ወደ በጌምድር ሔዱ። ይህ ሁኔታ የተቃውሞ ጦር ለማዘጋጀት ነው ተብሎ በእንደራሴው በንጉሥ ተፈሪ ስለተገመተ ንጉሥ ተፈሪ ራስ ጉግሣ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ የትዕዛዝ መልዕክት ላኩ። ራስ ጉግሣ ትዕዛዙን አክብረው ወደ አዲስ አበባ አልተመለሱም። በዚህ ምክንያት ንጉሥ ተፈሪ በደጃዝማች (በኋላ) ራስና የጦር ሚኒስትር ሙሉጌታ የሚመራ ራስ ጉግሣን አስገድዶ የሚያመጣ ጦር ከሸዋ ወደ ቋና ልዩ ስሙ "አንቺም" ወደ ተባለው ሥፍራ ላኩ። በሌላ ጐንም የራስ ጉግሣ ወሌን የቅርብ ዘመድ የታጠቁትን ጦረኛ ደጃዝማች አያሌው ብሩን ከመንግሥት ጦር ጋር በመተባበር በራስ ጉግሣ ላይ ቢዘምቱ ከጦርነቱ በኋላ "ራስ" ብለው በስሜኑ ግዛት ላይ የቤጌምድርን ግዛት ጨምረው እንደሚሾሟቸው ገልጸው በማባበል ከራስ ጉግሣ ጦር ጀርባ ደርሰው እንዲዋጉ በማድረግ ራስ ጉግሣን ለሞትና ድል መሆን አበቁ።*

ዝምድናውም የስሜኑ መስፍን ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ገብሬ የየጁውን የታላቁን ራስ አሊን ልጅ ወይዘሮ ጓሩትን አግብተው በወለዱት በራስ ወሌ በኩል ነው፡፡




*እናቴ እማሆይ በዓና ጥሩ ለኔ ዕድሜና ጤና ለመለመን ገዳም ለንቢታ ከመንገድ ስትመለስ*




ወደቀደመ ነገሬ ስመለስ፣ ይህን በተናገራት ጊዜ ከቤተ ክርስቲያኑ ደጀ ሰላም ጥግ ደርሰው ስለነበር እናቴ ምርር ብላ አዝናና ተቆጥታ ወደ ኪዳነ ምሕረት

ዝምድናውም የስሜኑ መስፍን ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ገብሬ የየጁውን የታላቁን ራስ አሊን ልጅ ወይዘሮ ጊፋትን አግብተው በወለዱት በራስ ወሌ በኩል ነው።



*እናቴ እማሆይ ቦሳና ጥሩ ለኔ ዕድሜና ጤና ለመለመን ገዳም ሰንብታ ከመንገድ ስትመለስ*

ደጃዝማች ኃይለ ማርያም

ቤተክርስቲያን እየተመለከተች ‹‹ኪዳነ ምሕረት! እኔን እንደ ሰው ፈጥረሽ ከሆነ፣ ላመት ልጅ ይዤ እንድመጣ አብቂኝ፤ ካልሆነ በውሻ ኩስ ታጠኚ›› ብላ ተሳለች፡፡ ስለቷ ደርሶ እኔ በመወለዴ በዓመቱ እኔን አሳዝላ ስለቷን እንዳገባች ደጋግማ አጫውታኛለች፡፡ ከአንድ ድርጊት ጀርባ የሚገኝ ቅድስና (በረከት) እንደሚባለው እሜቴ ዓለሜ ተወልጄ ሲያዩ ደግሞ እናቴ እንደነገረችኝ ‹‹ከአባትህ በበለጠ የእሜቴ ዓለሜን ባለቤት (አያቴን) ፊታውራሪ ባዩህን መሰለ›› ብለው ስለወደዱኝ እሳቸው ሲያሳድጉኝ ወሰዱኝ፡፡ እሜቴ ዓለሜና ፊታውራሪ ባዩህ ሁለቱም የአራቱ አምባራስ (የአራቱ ዙፋን) ተወላጆች እንደመሆናቸው በትውልድ እማይበላለጡ ቢሆኑም፤ እሜቴ ዓለሜ ወገናማ በመሆናቸው ጐልተው ይታዩ ነበር፡፡ በስሜን ያራቱ አምባራስ[3] ተወላጅ ለሆነ፣ ከሱ የሚበልጥ ባላባት አልነበረም፡፡ ወገኑ ብዙ፣ ኃይሉም ከባድ ነበር፡፡ የስሜን ሕዝብ ትውልድ የተጠላለፈ እንደመሆኑ ከባዕድ ዘመዱ ስለሚበልጥ የስሜን ሰው ለወንድሙና ለእግሩ[4] ግድ (ደንታ) የለውም ይባላል፡፡ በዚህ የተነሣ እንደ ቆለኛው ደም ሳይቃባ በሰላም ይኖራል፡፡

3 *አራቱ አምባራስ (አራቱ ዙፋን) ስለተባለው ትንሽ ልግለጽ፡፡ በአፈታሪክ ፈላሾች (ቤተ-እሥራኤሎች) ከአክሱም ተነሥተው ወደ ወልቃይትና ጠገዴ፣ ከዚያም እየገፉ ወደ ደጋው ወደ ወገራ እንደሔዱ ብዙ ጊዜ ይነገራል፡፡ ከዚያም ወደ ስሜን ሲዘልቁ ሲሉ አራት የክርስቲያንና አንድ የእስላም (ሙስሊም) መሪዎች ባላባቶች አንድ ግንባር ፈጥረው ይህን ስሜንን ለመውረር ከወገራ የተነሣ ጠላት በመውጋት አገራቸውን (ስሜንን) ከወረራ ለማዳን መስማማታቸውን ለንጉሡ ለዐፄ ዐምደ ጽዮን ያስታውቃሉ፡፡ ጌዲዮን የተባለው የፈላሾች መሪ ቋሚ መቀመጫውን ወገራ አድርጎ ስሜንን ሊወር ሲል፤ እነዚያ የአምባራስ ባላባቶች ተባብረው አንድ ላይ ሆነው ከፍ ያለ ጦር እንዳሰለፉ ይሰማል፡፡ በዚህ ጊዜ ጌዲዮን አንድ ሐሳብ ለንጉሡ ለዐፄ ዓምደ ጽዮን ያቀርባል፡፡ ሐሳቡም በግራ በቀኝ ብዙ ሠራዊት አሰልፈን ከምናጨራርስ አንድ ጀግና ከኛ በኩል፣ አንድ ጀግና ከናንተ በኩል ወጥተው ይፋለሙና የተሸነፈው ለአሸናፊው ይገዛ የሚል ነበር፡፡ ንጉሡ የጌዲዎንን ሐሳብ ከሰሙ በኋላ መክሬ መልስ እሰጥሃለሁ ብለው በቀጠሮ ተለያዩ፡፡ ይህን የሰማ አንድ የስሜን ሰው መጀመሪያ ካምባራሱ መሪዎች ቀጥሎም ንጉሡ ዘንድ ቀርቦ “የመጣ ይምጣ እፋለመዋለሁ፣ አሸንፌዋለሁም የቀረበውን ሐሳብ ይቀበሉ” ብሎ ይናገራል፡፡ ንጉሡ ነገሩ ከብዷቸው ስለነበር “ካሸነፍክማ ሲሦ መንግሥቴንም ቢሆን እሰጥሃለሁ” ይሉታል፡፡ ሰውዬው “የለም ሲሦ መንግሥትዎን ሳይሆን ሴት ልጅዎን ይሰጡኝ” ብሎ በመጠየቁ ንጉሡ ተስማምተው ከሰውየው ጋር ውል ይጨርሳሉ፡፡ ጌዲዮን ያቀረበውን ሐሳብ የተቀበሉት መሆናቸውን ለጌዲዮን፣ አራቱ ክርስቲያንና ለሙስሊሙ አምባራሴ ተጠሪዎች ገለጹ፡፡ በዚህ ውል መሠረት፣ የግራ ቀኙ ሠራዊት እንደተሰለፈ ሁለቱ ተፋላሚዎች ወደ መስኩ እንዲመጡ ተጠርተው ወጡ፡፡ ጌዲዮን የመለመለው ጐሊያድን የመሰለ ዝሆን የሚያህል ሰው ሲሆን፤ ከንጉሡና ከአምባራሶች ተመልምሎ የመጣው ግን ሩር (እንቁር) የሚያህል አጭር ሰው፣ በምንም ዓይነት ተፋላሚውን ይቋቋማል ተብሎ የማይገመት ነበር፡፡ የሆነ ሆኖ እችላለሁ ብሎ ለንጉሡ ቃል ሰጥቷልና ሊሞክር ቆርጦ ቆመ፡፡ የጌዲዮን ምልምል ተፋላሚውን ሲያይ ድሉ የሱ እንደሚሆን ተማምኖ ወዲያና ወዲህ እየተንጐማሸረ መስኩን ሞላው፡፡ ከዚያ አምባራሴውን ይዞ ቀለባጥሞ ለመጣል ሲያሳድደው፤ አምባራሴው ከአጠገቡ ደርሶ ሹልክ ሹልክ እያለ እያመለጠ የጌዲዮንን ተመራጭ እስኪናደድ ድረስ አደከመው፡፡ አምባራሴው ለመያዝ እንዳይመች ሰውነቱን በቅቤ ተለቅልቆ ነበር፡፡ ይሑን እንጂ በመጨረሻ የጌዲዮን ምልምል አምባራሴውን ያዘውና ሁለት እግሩን ባንድ እጁ አንገቱን በሌላው እጁ ይዞ ትከሻው ላይ አጋድሞ በግራ ቀኝ ሠራዊቱ መሐል እየተንጐማለለ ወደ ወገኑ መሔድ ጀመረ፡፡ በመካከሉ ግን አምባራሴው ከማተቡ ጋር አጣብቆ አስሯት የነበረች ምላጭ አውጥቶ፣ የተሸከሚውን ያንገት የደም ስር ቆረጠ፡፡ ያ ግዙፉ ሰው በድንገት ዘፍ ብሎ ወደቀና ድል የአምባራሶች ሆነ፡፡ በዚህ የተነሣ ስሜን አገሩና አገዛዙ ከሞላ ጐደል የአራቱ አምባራስ (የአራቱ ዙፋን) የክርስቲያኑና አንዱ ሙስሊም ባላባት ተወላጆች ሆኖ እስከ ደርግ መምጣት ድረስ ኖረ፡፡ ለድል አድራጊው አምባራሴም ንጉሡ ዐፄ ዓምደ ጽዮን ሴት ልጄን እሰጥሃለሁ ብለው በገቡት ቃል መሠረት ልጃቸውን ሰጡት፡፡*

4 *ዛሬ እግርን ማጠቡ ምን ያደርጋል? ነገ ተመልሼ ጭቃ ውስጥ ልገባ እያለ እግሩን በቅጭጭት ያስቆጣል*

እኔም የተወለድኩት ከአምባራሴዎቹ ወገን ሲሆን፤ በግርጌ ማስታወሻ ፲ እንዳሠፈርኩት የዐፄ ዐምደ ጽዮን ልጅ ከተሰጠችው አምባራሴ ከተወለዱት ልጆች በዘርፍ የተገኘሁኝ ነኝ። ይህም ማለት ዐፄ ዓምደ ጽዮን ልያ ድንግልን ይወልዳሉ። ልያ ድንግል የአምባራሴዎችን ተወካይ ተፋላሚ ሠርፀ ሥሉስን (ደጃዝማች ተብሎ) አግብታ አራቱን ዙፋን፣ ዳባን፣ ኪሮስን፣ ገላውዴዎስንና ክፍሎንን ትወልዳለች። ክፍሎን ፍሦንን፣ ፍሦን ስሜኖን (ትልቁን የስሜን መስፍን)፣ ስሜኖን አቤቶ ሄኖክን (አቶ ሄኖክም ይባሉ ነበር። በጊዜው ትልቅ ማዕረግ ስለነበር)፣ አቤቶ[5] ሄኖክ አቤቶ ዮናታንን፣ አቤቶ ዮናታን ወልደ ተክሌን፣ ወልደ ተክሌ ዓለሜን፣ ዓለሜ አስረሴን፣ አስረሴ እኔን ብርሃኑን ወለደ።[6]

በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በደረሰው የፋሽስት ወረራ ምክንያት ያምባራስና ያድስጌ ጉበዝ ሁሉ ለወረራ የመጣውን ጣሊያን ለመከላከል ወደትግሬ ዘመተ። ድል የጠላት ሆኖ ዘማች ወደ አገሩ ሳይመለስ ጠላት አምባራስንና አድስጌን (ለተንቤን ቅርብ ስለነበር) ወረረ። ከዚያ በመንደሩ የነበሩትን ባልቴት፣ ሽማግሌ፣ ሴትና ልጅ ይዞ ጐንደር ቁስቋም ወስዶ አሠረን። እሥራታችንም ከቤተክርስቲያኑ ስር ካለው ረባዳ መሬት ለፀሐይም ሆነ ለውርጭ የሚሆን ከላይ ከታች ከለላ በሌለበት ዙሪያውን በታጠረ መሬት ላይ ነበር። ቀለባችንም በነፍስ ወከፍ አንድ ቀን አንድ ጣሳ መኮረኒ አንድ ቀን አንድ ጣሳ ፍርኖ ዱቄት ነበር።

ምግቡን የምናዘጋጀውም በአጋጣሚ ያገኘነውን ገረወይና ለማቡኪያ፣ ክዳኑን ደግሞ እንደ ምጣድ ለመጋገሪያ በመጠቀም ነበር። የገረወይናው ክዳን ስስ ስለነበረ እህል የሚያሳርር በመሆኑ በአቅራቢያው የሚገኘውን ኮሽሽላ በማቃጠል ዓመዱን በስሱ ቆርቆሮው ክዳን ላይ በመነስነስ ቡሆውን ስናደርግበት የክዳኑን ሙቀት ያለዝብልንና የበሰለ ቂጣ ለማውጣት ይረዳናል። እዚህ በቆየንባቸው ሰባት ወራት ሁሉ አመጋገባችን እንዲህ ነበር። ከተወሰኑ ወራት በኂላ ቼቼላ መንደር ራስጌ ‹ጅንዮ› የተባለ የጣሊያን ጦር መንገድ ሥራ ድርጅት ሠፈር የነበረው ሲለቀቅ እዚያ እንድንገባ ተደረገ። የ ‹ጅንዮ› መንደር እኔን የተቀበለኝ በክፉ ነበር። እዚያ የገባን የዕለቱ ለት ጊንጥ ነድፎኝ ሌሊቱን ሙሉ ሳለቅስ አደርኩ። ከጥቂት ወራት በኂላ ነፃ ተለቀን ቼቼላ ከተባለው መንደር ገብተን መኖር ጀመርን። አርበኛው እየተጠናከረ ሲመጣ፤ አባቴ ወዳለንበት ቦታ ሰዎች ልኮ ቅዳሜ ቀን ከገብያተኞች ጋር ኀንበራ[7]

---

5 ስለዚህ ቃል ከአዛውንቱ የሰማሁት በስሜንም እንደ ሸዋው ቤተመንግሥት ሥርዓት በመሰለ መልኩ ጥቅም ላይ ይውል እንደነበር ነው የተረዳሁት።

6 በመኸል የዘለልኩት ቢኖር ያራቱ አምባራስ ልጆች በመናደድ ጠጉራችሁ አይቁም። በመዘንጋት እንጂ ሆን ብዬ ያደረግሁት አይደለምና።

7 ጋሳ አገር እየተባለ ይጠራ ወደ ነበረው፤ ኀንበራ የዐፄ ፋሲልን ፈረስ ለማገረም ከጐጃም ሜጫ ከተባለው ክፍል የመጡ ስልሳ አባውራ ኦሮሞዎች ይኖሩበት የነበረበት አገር ነው። እነዚህ ስልሳ አባውራዎች እየተዋለዱ ኑሮው ተመችቷቸው በጣም የሚያማምሩ ስለነበሩ ከአካባቢው ሕዝብ ጋር በመጋባት ተቀላቅለው የቀድሞው ዘር ፋራ ወይም አሻራ ጠፍቶ፤ ሁሉም ጐንደሬዎች ሆነዋል።

ተብሎ ወደሚጠራው ቦታ አዛወረን። ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ወደ ወገራና ወደ ስሜን ተወስደን ኑሯችን እዚያ ሆነ።

ጠላት እንደለቀቀ ያባቴ የመጀመሪያ ሹመት (ኃላፊነት)፣ ደባርቅ ከተማ ጉጢት ጉብታ ላይ ከነጭፍሮቹ ሰፍሮ ከጐንደር ወደ አሥመራ የሚተላለፉ አገሬው በልማድ ‹‹ጃንቦ›› የሚላቸው የምሥራቅ አፍሪካና በዚያው ስም የሚጠሩ የደቡብ አፍሪካ የእንግሊዝ የጦር አባላት መኪና ነጂዎች ላይ አገሬው ጓንዴ ጠመንጃ ለመዝረፍ እየተኮሰ አደጋ ያደርስባቸው ስለነበር፤ ወቅን ከሚባለው ተራራ አንስቶ እስከ ድብ ባህር (ሊማሊሞ) ያለውን አገር ከአደጋ ጣዮች መጠበቅና ማስተዳደር ነበር። ሁለተኛው ደግሞ መቀመጫችን ሸዋዳ ላይ ሆኖ ሸዋዳንና አካባቢውን ወደ ጽዮን ማርያም፣ ወደ አባ ሊባኖስ፣ ወደ እንጨት ካብ፣ ጨጓርና ሠጊ፤ በምዕራብ በኩል ደግሞ ወስከምቢትና ጋሻ መድፊያ በሰሜን ባሪታ ሆድን ጭምር ከወንበዴ መካካል፣ ጸጥታንና ሰላም ማስፈንን ያጠቃለለ የአስተዳደር ሥራ ነበር። አባቴ በተፈጥሮው ፈጣንና ወሳኝ ከንግግር እጁ የሚቀድም ስለነበር፤ ከበሳሉ ጦር ጋር ለአስቸኳይ ድርጊት የሚያውላቸው የጋሜ ጦር የሚባሉ ከአሥራ አራት እስከ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ገደማ ዕድሜ ያላቸው ወጣት ጦረኞች ነበሩት። እነዚህ የጋሜ ጦሮች እንደ ፖሊስ ያለ ተግባር እንደነበራቸው ከአደራጉታቸው ዓይ ነበር።

እኔም ወደ አባቴ ቤት (ቢሮ ስላልነበረ) በበቅሎ ተጉዘው የሚመጡ በቀን አራት ወይም አምስት የሚሆኑ እንግዶችን ሌላ ሰው ሳይቀድመኝ ሮጬ ከተቀመጡበት በቅሎ እንዲወርዱ በአንድ እጄ ልጓሙን በአንድ እጄ እርካቡን ይዤ አግዝ ነበር። እንግዶቹንም እንደ ማዕረጋቸው ጫማ ወይም ጉልበት ስሜ በቅሎዋን ወደ ጥላ ወስጄ ኮርቻውን ፈትቼ እዛው ላይ ትንሽ አናፍሼና አራግፌ መደላደሉንም አናፍሼ በማስቀመጥ አገለግል ነበር። ለበቅሎዋ ገፈራና ውሀ ሰጥቼ፣ እንግዶቹ ወዳረፉበት ሔጄ እግራቸውን አጥቤ ጫማ ስሜ መመለስም ተግባሬ ነበር። አብዛኛው እንግዳ ዘመድ፣ ወዳጅ ነው። ድርጊቴ ደስ ያላቸውም ወንዶቹ ‹‹ስትዳር እንዘፍንልሃለን፣ ስታገባ እጀ ጠባብ እንገዛልሃልን›› ይሉኛል። ሴቶቹ ደግሞ ‹‹ስታገባ ኩታ እፈትልልሃለሁ›› ይላሉ። አንዳንዳቹ ደግሞ ጉርሻ ብለው ከዝናራቸው ጥይት አውጥተው ይሸልሙኛል። ያኔ የጥይት ሽልማት ማግኘት ትልቅ ነገር ነበር።

የጥይት ነገር ከተነሳ ስለተኩስ አለማመዴም ማንሳት ጥሩ ነው። ብዙውን ጊዜ ወደ ማታ አካባቢ የወጣቶች የተኩስ ልምምድና ውድድር አለ። ወጣቶቹ ታዳጊ ልጆች ጥይት የምናገኘው ከሰው ብቻ አይደለም። ጥይት የምንገዛበት መንገድም ነበረን። ልጆች የቀይ ሽንኩርት (መጣፈጥ) መትከያ መደብ (ጉልማ) ስለሚሰጠን፤ መደቡን በደንብ አለስልሰን ሽንኩርት ተክለን እየኮተኮትን ያለተራችንም ጭምር ውሀ ከመስኖ ስርቀን እያጠጣን ቶሎ እንዲደርስ እናደርጋለን። ሲደርስ ነቅለን ደባርቅ ገበያ ተወስዶ ተሸጦ በተገኘው ገንዘብ ጥይት ገዝተን ተኩስ ውድድር ውስጥ እንገባለን። ሽመል ምከታ፣ እጅ ንጥቂያ፣ ትግል፣ ውሀ ዋና፣ በደጋው ደግሞ ፈረስ ግልቢያ

ከተኩስ ልምምዱ ጋር አብረው የሚሔዱ የታዳጊ ልጆች ግዴታዎች ነበሩ። ለተኩስ ልምምዱ ዒላማ የሚሆነው ነጭ አጥንቱ ብቻ የሚታይ የበሬ ግንባር ማዶ ይደረግና ግንባሩን በጥይት ለመምታት መሞከር ነው። መቼም ይሔን ወዲያውኑ ማድረግ አይሳካልንም። ከብዙ ሙከራዎች በኋላ ያቺን የበሬ ግምባር አጥንት ያገኘነው ቦታ ላይ መምታት እንጀምራለን። ቀጥለን ደግሞ በበሬው ግምባር ላይ የማርያ ትሬዛ ብር ያህል የምታክል ስፋት በቅጠል አቅልመን ያቺን ቦታ አስተካክለን ለመምታት መለማመድ እንይዛለን። ይሔንንም ከተወሰነ ሙከራ በኋላ መፈጸም እንችላለን። ለምነንም ሆነ አንዱን ዘመድ አስተኩሰኝ ብለን ጫማ ስመን ያገኘነውን ጥይት የምናውለው ለዚህ ዒላማ ተኩስ ነበር።

ወደዒላማ ተኩስ ከመድረሳችን በፊት ብዙ የምናልፋቸው ፈተናዎች ነበሩ። ለምሳሌ መጀመሪያ የተኩስ ድምፅ ከመልመዳችን በፊት ደንግጠን ከነበርንበት ሸሽተን እቤት ድረስ እንሮጥ ነበር። የተኩስ ድምፅ እንድንለምድ ከሚተኮስበት ቦታ መቶ ሜትር ርቀን እንድንቆም ይደረግና ሲተኮስ ከዛ እየሮጥን ወደቤት እንገባ ነበር። በዚህ ርቀት የሚፈጠረውን ድምፅ ስንለማመድ ደግሞ ተኩሱን ከሚተኩሱ ሰዎች ሰላሣ ሜትር ያህል ለተኳሹ ቀርበን እንድንቀመጥ ይደረጋል። ተኩሱ ሲተኮስና ድምፁን ስንሰማ ደንግጠን ተፈንግለን እንወድቃለን። አንዳንዴም፣ ትልልቆቹ ይኸ ፈሪ ብለው እንዳይናገሩብን በመፍራት እዚያው እንደረጋን ሆነን ድፍረታችንን ለማሳደግ እንሞክራለን። የተኩሱን ድምፅ ስንለምድ ደግሞ ከተኳሹ ኋላ ተቀምጠን ወገቡን በሁለት እጃችን አጥብቀን ይዘን ሰውነታችን እየተንቀጠቀጠ ‹‹ድው›› ሲል በፍርሃት ተኳሹን ወደ እኛ ስበን ተያይዘን የኋሊት መሬት ላይ እንንጋለላን። ከዚያ በኋላ ከፊት በኩል ከተኳሹ ጭን መኸል እንቀመጥና ጠመንጃው ትከሻችን ላይ እየተደገነ ሲተኮስ በድምፁ ድንጋጤ ተኳሹን ገልብጠን እንጥለዋለን። ቀጥሎም የጠመንጃውን ሰደፍ ከደረታችን ላይ ወድረንና ክብደቱን ችለን አፈ ሙዙን ከባላ እንጨት መኸል በማስገባት በተቻለ ትንፋሻችንን እንድንውጥ እየተደረገ እንተኩሳለን። እንዲህ እያልን አነጣጥሮ መተኮስን በልጅነታችን እንለማመድ ነበር።

እንዲህ እያደረኩ ከ፲፱፻፷፬ - ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የነበረውን ጊዜ አሳለፍኩና በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ያልታሰበ ነገር ቤተሰቡን ገጠመው። ነገሩ እንዲህ ነው። ራስ እምሩ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የቤገምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት ገዥ ስለነበሩ አዲስ ግብር ጣሉ። የጣሉት አሥራትና ግብር ከበደን በማለት የስሜን ሕዝብ ሸፈተ። ከዚህ ዐመፅ ጋር በተያያዘ አባቴ ከዐመፀኞች አንዱ ተብሎ ተይዞ አዘዞ በአንደኛ ሻለቃ ጦር ሠፈር ክልል ውስጥ (ወደ ተክለ ሃይማኖት ቤተክርስቲያን መሔጃ አጠገብ ካሉት ፎቆች በአንደኛው ውስጥ) በጦር ሠራዊት እንዲጠበቁ በመደረጉ የእኔንም ሕይወት የሚቀይር አጋጣሚ ተፈጠረ። ምክንያቱም ከጦር ሠራዊት ልጆች ጋር ተማሪ ቤት ገብቼ ጥቁር ሠሌዳ ላይ ፊደል እየተጻፈልን ሀ-ሁን መቁጠር ጀመርኩ። ከዛ ውጭ ድማዛ ወንዝ ላይ ባለው ድልድይ ላይ የብርጭቆ ቂጥ በሚመስሉ ጠርሙሶች አንዱ አዘዞ ሌላው

ጐንደር የሚሉ አቅጣጫ አመላካች ቀስቶች ላይ የተጻፉትን የእንግሊዝኛ ፊደላት በማንበብና በመጠየቅ ደግሞ ከፊሉን ኤቢሲ ለየሁ። አባቴና አብረው የተያዙት ሰዎች አሥራት ወደ ቁም እሥር ሲለወጥ አዘዞን ለቀን ቼቼላ ወደ ነበረው ቤታችን ገባን። ጐንደር ቤት አግኝተን እስክንሔድ ድረስ ቼቼላ ቆየሁ።

በዚህ ጊዜ እዚህ አካባቢ የነበሩ አራት ጓደኞቼ አባቶቻቸው ጐንደር በአታ ማርያም ቅጥር ይሠሩ ስለነበር፤ ላባቶቻቸው ምሳ ሊያደርሱ ከቼቼላ ወደ በአታ ማርያም ሲሔዱ እኔም አብሬ እሔድ ነበር። ከእነዚህ ቀናት በአንዱ የጓደኞቼ አባቶች ካሉበት እንደደረስን ከቤተ ክርስቲያኑ ትንሽ ፊቅ ብሎ የልጆች ጫጫታ በመስማቴ ሁኔታው ጉጉት አሳደረብኝ። በሌላኛው ቀን ጫጫታው ምን እንደሆን ለማወቅ ካብ ለካብ እየተንኳተትኩ ሔጄ ከትምህርት ቤቱ መግቢያ አጠገብ ደርሼ ላይ፤ ተማሪዎቹ በአራት አምስት ያህል ቡድን ሆነው ትምህርታቸውን ሲያነበንቡ ዓየሁኝ። እነሱም ዓዩኝና ወደ ውስጥ እንድገባ በእጃቸው ጠቀሱኝ። እንዳይመቱኝ እየተጠራጠርሁ ገብቼ ቆምኩ። መምህሩ ሲያዩኝ ጠሩኝና ሳሙኝ። ሁኔታዬን ሲመለከቱ ከተማሪዎቻቸው የተለየሁ መሆኔን ልብ አሉ። አለባበሴ ወታደር ነክ፣ እጅጌው ጉርድ የሆነና የአሥር አለቃ ምልክት ያለበት ኮትና ቁምጣ ሱሪ፤ ጠጉሬ ሽለላ፣ አቋሜም ንቁ በመሆኑ ገርሟቸው «ና! በል እዚህ ተቀመጥና ተማር» ብለው አስቀመጡኝ። እሺ ብዬ ቁጭ አልኩኝ። ከተማሪዎቹ መካከል አንዱን ለኔ መደቡልኝና በብራና የተጻፈች የፊደል ማስተማሪያ ይዞ መጥቶ በአንዷት ግር እየጠቆምኩ አዘዞ ትምህርት ቤት ገረዳድፌ የነበረውን ፊደል አሁን ሳጠራ ዋልኩ፡፡ ወደ ማታም ጓደኞቼ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ እኔም ወደ ቤቴ ተመልሼ የዋልኩበትን ተናገርኩ፡፡ በማግሥቱ ከልጆቹ ጋር አብሬ እዚያው ተማሪ ቤት ሔጄ ዋልኩ፡፡ በማከታተልም ሁለትና ሦስት ቀናት ጾሜን እየዋልኩ ተማርኩ፡፡ በኋላ ምሳዬን ቋጥሬ መሔድ ጀመርኩ፡፡ ሳምንት ካለፈኝ በኋላ የሦስትና አራት ቀናት ቀለብ እየቋጠርኩና ያንን እየቆጠብኩ በመመገብ እዚያው ዜማ ሲማሩ ከሚያድሩት ጋር ሆኜ እኔም ማታ ማታ ውዳሴ ማርያምን ማውረድ ጀመርኩ። ትምህርቱ የሚቀርበው በግዕዝ ነበር። እኔም ፊደልን አጣርቼ ጨረስኩና ወደ ፊደለ ሐዋርያት ገባሁ።

በዚህ ላይ እንዳለሁ፤ አባቴ ጐንደር በደጃዝማች አምባቸው አጋፋሪ ቀኛዝማች መንግሥቱ መኖሪያ ግቢ ቤት አገኘና ተከራይተን ገባን። የቀኝ አዝማች መንግሥቱ ልጅ፣ ጥሩ መንግሥቱ (በኋላ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበሩት የጄኔራል ታፈሰ አያሌው ባለቤት የሆነችውም) በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት[8] የዘመናዊ ትምህርት ተማሪ ነበረች። እኔ የማላውቀውን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስትናገር ሰማኋት። በዚያ ላይ ደግሞ ብዙ ደብተር ትይዛለች። ይህን ሁሉ

8 ይህ ትምህርት ቤት የተከፈተው በ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. ነው። ከእርሱ በፊት ግን ከጃን ተከል ዋርካ ዝቅ ብሎ ከ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. የተከፈተ ትምህርት ቤት ነበር። የዚህ ትምህርት ቤት ተማሪ ከነበሩት አቶ አበሀይ አረፋይኔ የተባሉት ዕውቅ የሕግ ባለሞያ አሁንም በሕይወት ይገኛሉ።

ከየት አመጣችው ብዬ እየተገረምኩ፣ ሁኔታውን ለማወቅ ትንሽ እራቅ ብዬ ከኋላዋ መከተል ጀመርኩ። ለካስ እሷ የምትሔደው ወደ ተማሪ ቤት ኑሮ፣ ግቢ ውስጥ ገብታ ቀድመው ገብተው ከቆዩዋት ኩታራዎች[9] ጋር ተርታ ይዛ ስትቆም ዓየኋት። ከዚያን ቀን በፊት እንዲያ ያለ ነገር ዓይቼ አላውቅም ነበር እና በግቢው ውስጥ የሚሆነውን ሁሉ መከታተል ጀመርኩ። የጸሎት መጽሐፍ ተነቦ ሲያበቃ መዝሙር ተዘምሮ ሰንደቅ ዓላማ ተሰቀለ። ከዚያም ተማሪው ሳይጋፋ ተራውን ጠብቆ ወደ ክፍል ገባ። ይህ ሁሉ ሲሆን እኔ ከግቢው አጥር ውጪ ሆኜ ነበር የማየው። ተማሪው ሁሉ ገብቶ እንዳበቃ እደጅ ቆሞ የነበረ ፈረንጅ እንድገባ በእጅ ምልክት ጠራኝ። ሳልሄድ ቀረሁ። በኋላ የትምህርት ቤቱን ጸሐፊ ልኮ አስጠራኝ። ‹‹አይ እኔ ጣልያን አልወድም፣ አልገባም›› አልኩት። ይህን የሰማው ፈረንጅ ገርሞት ‹‹ጣሊያን አይደለም በለው›› አለ። እኔ ግን አገረገርኩ። ለካስ ፈረንጁ አሜሪካዊ የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ኑሯል። ‹‹እኔ እሸሽጋለሁ፣ በሌለሁበት አምጣና አስገባው›› ብሎት ጸሐፊው መጥቶ ይዞኝ ወደ ውስጥ ገባና መጋቢት እኩሌታ ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. ጀማሪ ክፍል ተመዝግቤ ትምህርት ጀመርኩ።

በትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ከክፍል አንደኛ ወጣሁ። በዚህ ጊዜ ትምህርት ሚኒስቴር ተማሪውን ለማበረታታት ከየክፍሉ አንደኛና ሁለተኛ የወጡ ተማሪዎችን በአውሮፕላን ለማንሸራሸር በአንድ መኪና አሳፍሮ የአየር መንገዱ ጽሕፈት ቤት ወዳለበት ወደ አውሮፕላን ማረፊያው ወስደውን ስንደርስ በሰልፍ እንድንቆም ተደረግን። ከዚህ ጊዜ በፊት አውሮፕላን በቅርብ አይቼ አላውቅም ነበር። አውሮፕላኑ ከአዲስ አበባ መጥቶ ምድር ከነካ በኋላ ቀጥታ ወደኛ ሰጦ ሲመጣ፣ ከጽሕፈት ቤቱ ጋር ሊያጋጨን ነው ብለን ፈርተን አብዛኞቹ ከዛ ሮጠን ጫካ ውስጥ ገባን። አውሮፕላኑ እንደቆመ ከየተደበቅንበት እየተፈለግን ተጠርተን ወደነበርንበት ተመለስን። በእንዲህ ያለ ሁኔታ በኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን ተሣፍረን ለሃያ ደቂቃ በአውሮፕላን ጐንደርን ዞረን እንድናይ ተደረገ። ይህ ድርጊት ተማሪውን ለማበረታታት ብቻ ሳይሆን፣ የአገሩን ሰውም በአውሮፕላን መጓጓዝን ለማስለመድ ጭምር ታስቦ ነው።

እኔ እራተኛ ክፍል እስክደርስ ድረስ ጠዋት ተማሪው በሰልፍ በየክፍሉ ይቆምና አለቃ ምሕረቱ ቸኮል የተባሉ መምህር ከመጽሐፍ ቅዱስ የዕለቱን ምንባብ አውጥተው ያነባሉ፡፡ ቀጥሎም ‹‹አባታችን ሆይ›› የሚለው ጸሎት ተጸልዮና የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ተዘምሮ ወንዱ ወደ ወንዱ፥ ሴቱም ወደተለየ የሴቶች ክፍሉ ሔደው ለየብቻ ነበር የምንማረው፡፡ አለቃ ምሕረቱ ቸኮል በሌሉባቸው ቀናት እርሳቸውን ተክተው ሥርዓቱን የሚመሩት መምህር ምን ተሰኖት የሚባሉ ካህን ነበሩ፡፡ በኋላ አለቃ ምሕረቱም ሆኑ መምህር ምን ተሰኖት


9 ልጅ ለማለት ነው፡፡

ማንበባቸው ቀርቶ ተማሪ ያንብብ የሚል ፕሮግራም ወጣና፣ አምስተኛ ክፍል የነበረ ታፈሰ ተክሌ የተባለ ተማሪ በየዕለቱ እንዲያነብ ተደረገ፡፡ እሱ ብቻ ሲያነብ ቆይቶ በመካከል ደግሞ እሱ ያልተገኘ እንደሆነ እኔ ከአራተኛ ክፍል ወጥቼ እንዳነብ ተደረገ፡፡ አምስተኛ ክፍል ስደርስ ታፈሰ ተክሌ ስድስተኛ ክፍል ስለሆነ አስቸኳይ የመምህራን ፕሮግራም ተብሎ ስለወጣላቸው በዚህ ምክንያት መቅረት ስላበዛ እኔ በቋሚነት ማንበብ ጀመርኩ፡፡




*ጐንደር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት ሳለን፤ ቁጥር ፩ እኔ፣ ቁጥር ፪ ኮሎኔል መንግሥቱ ወደሴንያ ሊሌዱ አውሮፕላኑን ሲያበሩ ነበሩት ኮሎኔል መኮንን አዴላ፣ ቁጥር ፫ የእኔ ምክሼ ብርሃኑ ሐሚድ፣ ቁጥር ፬ በአገሪቱ ብቸኛ የድልድይ መሐንዲስ ሺፈራው*

አምስተኛ ክፍልን በሙሉ እኔ ካነበብኩ በኋላ ስድስተኛ ክፍልን ላጋምስ ስል፣ ፕሮግራም ተለወጠና ከኔው ክፍል ፋሲል ውብነህ የተባለ የአቶ አያሌው ደስታ የትምህርት ቤቶች ሥራ አስኪያጅ ዘመድ የነበረ፣ ሽፈራው ገዛኸኝ የተባለ የሴቶች አዳሪ ትምህርት ቤት ሞግዚት የነበሩት እመቤት ልጅ፤ መኮንን አደላ (በኋላ ኮሎኔል ሊቀመንበር መንግሥቱን ናይሮቢ ያደረሰው አውሮፕላን አብራሪ) እኔን እየተኩ እንዲያነቡ ተደረገ፡፡ ቆይቶ ደግሞ ከኛ በታች አምስተኛ ክፍል ከነበሩት አብዛኞቹ ተክተው ማንበብ ጀመሩ፡፡ ከእነርሱ መኻል (በኋላ በመጀመሪያ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ቀጥሎም የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አዘጋጅና ደራሲ የነበረው) ብርሃኑ ዘሪሁንም ይገኝበት ነበር፡፡ ከሱ ቀጥሎ የሱ ክፍል ተማሪ ሙሉጌታ ዘሪሁን የተባለ ልጅ አልፎ አልፎ ያነብ ነበር፡፡ ባብዛኛው ግን



ኃይለ፡ሥላሴ፡
ትምህርት፡ቤት፡
፩
፪
፫
፬

ከአራተኛ ክፍል አጋማሽ እስከ ስድስተኛ ክፍል አጋማሽ በነበረው ጊዜ አነብ የነበርኩት እኔ ነኝ፡፡

በዚህ በአዲስ ኪዳን ንባብ ብቻ ሳይሆን በትምህርት ቤቱ እግር ኳስና ቤዝ ቦል ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም በመዝሙርና በቲያትር ጠንካራ ተሳታፊ ነበርኩ። ከነበርነው የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ሽፈራው ገብሩ (በኋላ በአውራ ጐዳና የድልድይ መሐንዲስ) ከሁላችን በዕድሜም በሰውነትም ትንሽ ቢሆንም፤ በቤዝ ቦል ኳስ ምት ከማንኛችንም ጐልቶ የሚታይ ነበር። በቡድን ስንካፈል፣ ሌላ ሽፈራው የሚባል ተማሪ ስለነበር ሁለቱን ለመለየት ትንሹን ‹ማይቲ ሽፈራው› እያልን እንጠራው ነበር። የስም ነገር ከተነሳ እኔንም ብርሃኑ ሐሚድ ከሚባለው ተማሪ ለመለየት ‹ብርሃኑ ዘግሬት› የሚል ስም ወጥቶልኝ ነበር። የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ቤት ስገባም በስፖርቱ ተሳታፊነቴ ገፋሁበት። በተለይ ካፒቴን እስካነን (በኋላ ሜጀር) መጀመሪያ የክብር ዘበኛ ቀጥሎም የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች የስፖርት ኃላፊ የነበረ፣ ሚስተር ሃርቲንግ የተባለ የካፒቴን እስካነን ጓደኛና የተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት የስፖርት አስተማሪና ካፒቴን ጉስታቭ ፎርስ ማርክ (የስዊድን ንጉሣዊ ቤተሰብ) የሚባል በአየር ኃይል አሠልጣኝ የነበረ ስዊድናዊ በተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት የስዊድን መንግሥት ቤተሰብ በሚያዘጋጇቸው የተለያዩ የስፖርት ውድድሮች ተማሪዎች እንድንሳተፍ ሁኔታዎችን አመቻችተው ያደረግነው ውድድር አይረሳኝም። በፒንግፖንግ (የጠረቤዛ ኳስ) ለመጨረሻው ማጣሪያ ግጥሚያ የደረስነው እኔና ለካፒቴን ፎርስማርክ ነበርን። በዚህ ግጥሚያ እኔ ሰውነቴን አስቆጥቼ ስጫወት የተመለከተኝ ካፒቴን ፎርስማርክ ዘና ብዬ ኳሷን ዓይቼ እንድመልስ ሲነግረኝ እኔ ደግሞ አለመጠቃትን እንጂ ካፒቴኑ የሚለውን ተቀብዬ መጫወትን ሳልቀበል ቀረሁ። በዚህ ምክንያት ውጥረት ነግሦ በማየቱ እማሽንፍ መስሎት ተናደደና ጨዋታውን ጥሎ ሔደ። ስለዚህ በጨዋታው እኔ አሸነፍኩ።

ከጠረጴዛ ቴኒሱ በተጨማሪ በትምህርት ቤቶች ዓመታዊ የስፖርት ውድድር ጊዜ ትምህርት ቤቴን ወክዬ በስምንት መቶና በአንድ ሺህ አምስት መቶ ሜትር ሩጫም እሳተፍ ነበር። ቢሆንም የመድኃኔ ዓለም ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሆኑ የቦረና ልጆች እነ ሁሴን ሮበሌን የመሳሰሉ ረጅም ቁመት ያላቸውና ጠንካራ ሯጮች ነበሩና ሁለቱንም ዓመት ስሳተፍ በአንዱም አላሸነፍኩም።

በቀለሙ ትምህርት ፭ኛ ደረጃ ሳለሁ ዓመት ሳልጠብቅ ከክፍል ወደ ክፍል የመዘዋወር ዕድል እያገኘሁ በ፲፱፻፴፪ ዓ.ም. የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን (በጉንደር የአንደኛ ደረጃ መጨረሻ ክፍል የነበረው ስድስተኛ ክፍልን) አጠናቀቅሁ። በዘመኑ የትምህርት ሚኒስቴር ለአንደኛ ደረጃ ማጠቃለያ ፈተና የሚሰጠው በግንቦት ወር ነበር። ነገር ግን የጉንደር የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ስድስተኛ ክፍል ስለነበርና ሰባተኛ ክፍል ስላልነበረው የአንደኛ ደረጃ ማጠቀለያ ፈተና አይሰጠውም ተብሎ ታገደ። ከጥቂት ወራት በኋላ ውሳኔው ተለውጦ፤ በክፍል ከነበርነው አሥራ

አምስት ተማሪዎች ከፍተኛ ማርክ የነበረን የመጀመሪያዎቹ አሥር ተማሪዎች ተመርጠን ፈተናውን እንድንወስድ ተደረገ። በጳጉሜ ፈተናውን ከወሰድነው አሥር ልጆች መካከል፣ በክፍል እኔ አንደኛ ስሆን ሦስተኛ ይወጣ የነበረው ልጅ፣ አስካል (በኋላ ዮፍታሔ) ከበደ (በደርግ ጊዜ የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበረው) በፈተናው ከመቶ አምሣ (፶%) አግኝቶ ሲያልፍ እኔ ከመቶ አርባ ዘጠኝ (፵፱%) በማግኘቴ ወድቀኸል ተብዬ ቀረሁ። ዮፍታሔ ከበደ ብቻውን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወደ አዲስ አበባ ሔደ።

ባለፈው በደረሰብን በደል ከሃዘናችን ሳንወጣ በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም. ደግሞ፣ በጐንደር የአንደኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ሰባተኛ ክፍል ነበር። በሌላው አገር ግን ስምንተኛ ክፍል ነበር። ይህን በዓመቱ የትምህርት መጀመሪያ ጊዜ ማስተካከል ሲገባ በችልታ ተቆይቶ አሁንም የአንደኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናው በግንቦት ወር መስጠቱ ቀርቶ በጳጉሜ በመሆኑ ተማሪው ሁሉ ለዕረፍት በየቦታው ተበታትኖ ነበር። ስለዚህ እንደገና ተማሪው በጳጉሜ እንዲሰበሰብና ፈተናው እንዲሰጥ ሲደረግ፤ አማረ ገብረ እግዚአብሔር የተባለ ጐበዝ ኤርትራዊ ተማሪ በወቅቱ ሳይገኝ ቀርቶ ፈተናው አመለጠው። ሌሎቻችን ፳ ተማሪዎች ፈተናውን ወስደን አሥራ አምስታችን አልፈን መስከም ፳፬ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ.ም. አዲስ አበባ ገባንና ከአሥራ አምስታችን አምስቱ ተግባረ ዕድ አሥሩ ምኒሊክ ትምህርት ቤት ተደለደልን። እኔም ተግባረ ዕድ ከገቡት አምስቱ ተማሪዎች አንዱ ሆንኩኝ።

ከዚያ በተደለደልኩበት ትምህርት ቤት የሚሠጠውን የሦስት ዓመት የቀለምና የሞያ ትምህርት ማገባደጃ ላይ ስቃረብ፤ በግንቦት ወር፣ ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. በአሜሪካው ፕሬዝዳንት በፕሬዝዳንት አይዘን ሐወር የክብር ጥሪ፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አሜሪካንን ለመጎብኘት ሔዱ። በዚህ ጊዜ አዲስ አበባ የሚገዳው የአሜሪካ ኤምባሲ የዐፄ ኃይል ሥላሴን የአሜሪካ ጉብዓት አስመልክቶ አንድ መቶ ስማንያ ቅጂ ዕለታዊ መግለጫ (ኒውስ ቡለቲን) በእንግሊዘኛ ብቻ በእስቴንስል ጽፎ በማባዣ እያባዛ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ባለ ሥልጣኖች ያሠራጭ ነበር። ሥራውን አሻሽሎ ለማስኬድ በሬዲዮ ቴክኒሽያንነት (ኤሌክትሮኒክስ) የሠለጠነ ደህና የእንግሊዘኛ ችሎታ ያለው አንድ ተማሪ እንዲሰጠው የተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ዳይሬክተርን ጠየቀ። ዳይሬክተሩም የእንግሊዝኛ ትምህርት መምህራን የሆኑትን ዶ/ር ፍሌቸር[10] እና ተባባሪያቸውን መምህርት ሚስስ ሉዊስን[11] መስፈርቱን ያሟላል የሚሉትን ተማሪ መርጠው እንዲያሳውቁ ጠየቁ። ሁለቱም መምህራን እኔን መርጠው አሳወቁ። በዚያን ጊዜ እኔ በሬዲዮ ቴክኒሽያንነት (ኤሌክትሮኒክስ) ትምህርቴን ጨርሼ ልመረቅ ሁለት ወራት ቀርተውኝ ነበር። ዳይሬክተሩ ይህን መግለጫ ከመምህራኑ እንዳገኙ እኔን

---

10 ቀደም ብሎ የመድኃኔ ዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር የነበሩና በኋላ የመሐንዲስ ኮሌጅና የተግባረድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር የሆኑት፤

11 የመሐንዲስ ኮሌጅ ዲን ባለቤት የሆኑትን፣

አስጠርተው በደስታ ጉዳዩን ካስረዱኝ በኋላ ሁኔታውን በደብዳቤ ገልጸው ደብዳቤውን አሜሪካ ኤምባሲ ወስጄ እንዳደርስ ላኩኝ።

ደብዳቤውን ያደረስኩ ዕለት ሁለት የኢምባሲው ሹማምንት ወዳለሁበት መጥተው ላጭር ጊዜ አነጋግረውኝ ይመጥናል ብለው አምነው ነው መሰል፣ ለሦስት ወራት የሙከራ ጊዜ ተቀጠርኩ። በኤምባሲው ዕለታዊ ጋዜጣ ማዘጋጃ ክፍል፣ አጫጭር ትርጉምና የሥዕል የግርጌ መግለጫዎች ትርጉም ሥራና ዕለታዊው መጽሔት በአድራሻው በትክክል በፖስታ ታሽጐ መግባቱን፣ ከዚያም በየአድራሻው መሰራጨቱን የመቆጣጠር ተግባር ተሰጥቶኝ ሥራ ጀመርኩ። በዚያን ጊዜ በምሳ ሰዓት ከግቢው ወጥቼ ምሳ ልብላ ብል ከአምቦ ውሀ ጋር በቀን ከብር እስከ ብር ተኩል ያስፈልጋል። በየቀኑ የማወጣው ያን ያህል ገንዘብ ስላልነበረኝ ከሥራ ቦታዬ በመቆየት ዕለታዊ ጋዜጦችን (ቡሌቲንስ) አጠናቅቄ ባድራሻ አመልካቾቹ አምቦሎኮች እከታለሁ። ስለዚህ አዳዮቹ ሹፌሮች ከምሳ ሲመለሱ ጊዜ ሳያጠፉ የታሸጉ አምቦሎኮቹን ይዘው ይወጣሉ። እኔ እንዲህ የማደርገው በገንዘብ አቅሜ ውስንነት ተቸግሬ ነበር። ኃላፊዎቼ ደግሞ የትጉህ ሠራተኛነት ምግባር ሳይመስላቸው አልቀረም፤ የሦስት ወር የሙከራ ጊዜ ቅጥሬ ሊጠናቀቅ ሁለት ሳምንት ሲቀረው ቋሚ ሠራተኛ ሆነህ «የደመወዝ ማስተካከያ ጭማሪ ተደርጎልህ ወደ አሜሪካ ማስታወቂያ (ዩ.ኤስ.አይ.ኤስ) የፊልም ላይብራሪው ኃላፊ ሆነህ ተዛውረሃል፣ እንኳዋን ደስ አለህ።» የሚል ደብዳቤ ተሰጠኝ። ቋሚ ሠራተኛ መሆኔ ብቻ ሳይሆን የተቆረጠልኝ ደሞዝ ጓደኞቼ ከተቆረጠላቸው ደሞዝ እጥፍ ሊሆን የተቃረበ ስለሆነ፤ በጣም ደስ አለኝ። ከዚያም መሥሪያ ቤቱ ይገኝበት ወደነበረው ደጎል አደባባይ ከሚገኘው ከንግድ ባንክ ፎቅ አድርሰው ከሠራተኞቹ ጋር አስተዋውቀውኝ ሥራ ጀመርኩ።

እኔ ይህን ሥራ ስጀምር፣ በአዲስ አበባ ከተማ የነበሩት የሕዝብ መዝናኛ ስኒማ ቤቶች ሦስት ብቻ ነበሩ። ከነሱ ቀጥሎ የሕዝብ መዝናኛ ድርጅቶች የሚገኙት በአሜሪካ ማስታወቂያና በእንግሊዝ ማስታወቂያ መሥሪያ ቤቶች ነበር። ተፈላጊነቱና ተወዳጅነቱ እንደላይኞቹ አይሁን እንጂ የመስከብ የማስታወቂያ መሥሪያ ቤትም ዝቅተኛውን ኅብረሰብ ያገለግል ነበር። አራት ኪሎ በወቅቱ ወ.ወ.ክ.ማ የሚባለው ድርጅትም እንዲሁ በውሱን አቅም በመዝናኛነት ያገለግል ነበር። የአሜሪካ ማስታወቂያ (ዩ.ኤስ.አይ.ኤስ.) የተባለው መሥሪያ ቤት ዐላማው አሜሪካንን ማስተዋወቅ ነበር። መሥሪያ ቤቱ ሁለት ክፍሎች ነበሩት። እነርሱም የቤተ መጻሕፍት ክፍሉ (ላይብራሪው)፣ በአቶ ነጋሽ ገብረ ማርያም (በኋላ የአዲስ ዘመንና የኢትዮፊያን ሔራልድ ጋዜጦች አዘጋጅ በነበረው) የሚመራውና የፊልም ላይብራሪው (የኦዲዮ ቪ ዥዋል ክፍሉ) የአሥራ ስድስት ሚሊ ሜትር (የሲኒማ ቤቶች ፕሮጀክተሮች ሰላሣ አምስት ሚሊ ሜትር ናቸው) የተንቀሳቃሽ ፊልም ማሳያ ፕሮጀክተር፣ የሙዚቃ ሸክላና ማጫወቻዎቹ፣ ቴፕ ሪከርደር እንዲሁም የድምፅ

ማጉያ(ፓብሊክ አድሬስ ሲስተም) መገልገያዎችን የያዘው እኔ እንድመራው የተመደብኩበት ክፍል ማለት ነው።

ይህ ክፍል ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ለማሠልጠኛ ተቋሞች፣ ለተለያዩ የጦር ክፍሎች፤ ለፖሊስ፣ ለማዘጋጃ ቤቶች አስተዳደር ማሠልጠኛ ተቋም ወዘተ. ለማገልገል የተደራጀ ነበር። በዚህ ክፍል አሜሪካንን በስፋት የሚያስተዋውቁ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ፣ በፖለቲካ፣ በታሪክ፣ በአስተዳደር፣ በፍልስፍናና በሳይንስ፤ እንዲሁም በቴክኖሎጂ፣ በእርሻ፣ በግድብ ሥራ፣ በመስኖ ሥራ፤ በውትድርናም በአየር፣ በየብስና በባህር ጦር አደረጃጀትና ዝግጁነት ... ወዘተ. የሚያስተምሩ፣ የሚመክሩና የሚያዝናኑ፣ በቁጥር ከሦስት መቶ ሃምሳ በላይ በሆኑ በልዩ ልዩ የሙያ ዘርፍ ርእሶች በታላላቅ የመንግሥትና የጦር መሪዎች የተዘጋጁ ዶክሜንተሪ ፊልሞችና ... ወዘተ. መገልገያዎች የተደራጁ ነበር። በነዚህ መሣሪያዎች ለመጠቀም ክፍሉ ከላይ ከተጠቀሱት ተቋሞችና ከሌሎችም መሥሪያ ቤቶች በደብዳቤ የተላኩ ተወካዮችን ተቀብሎ መጀመሪያ ስለመሣሪያዎቹ አያያዝና አጠቃቀም የጥቂት ቀናት ሥልጠና ይሰጣል። ከዚያ ሥልጠና የተሰጣቸው ተወካዮች እነዚህን መገልገያፊች በተለይ ፕሮጀክተርና ፊልሞችን ተውሰው ወስደው ለመጡባቸው ተቋሞች ፊልም ያሳዩ ነበር። ተንቀሳቃሽ ፊልም በዚያን ጊዜ በጣም ብርቅ ነበር።

‹‹የዐፄ ኃይለ ሥላሴ የአሜሪካ ጉብኝት» የሚለው ፊልም ፺ ደቂቃ የሚፈጅ የጃንሆይን ሙሉ የአሜሪካ ጉብኝት የሚያሳይ ሲሆን፤ ‹‹የቃኘው ሻለቃ በኮሪያ» እና «ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት»[12] የተሰኙት ፊልሞች ደግሞ እያንዳንዳቸው አሥር አሥር ደቂቃ የሚፈጁ ነበሩ። «የቃኘው ሻለቃ በኮሪያ» የሚለው ፊልም ከአንደኛ እስከ አራተኛ ዙር ወደ ኮርያ የዘመተው የቃኘው ሻለቃ ጦር የዋለበትንና የፈጸመውን ጀብዱ የሚያሳይ ነበር። ፊልሞቹ ለሕዝብ ዕይታ ከመለቀቃቸው በፊት መጀመሪያ በአሜሪካ ኤምባሲ በአምባሳደሩ መኖሪያ ቤት፣ ሃያ ለሚሆኑ ዲፕሎማቶች እና የመንግሥት ባለስልጣኖች ታይተዋል። በመቀጠልም ሰባ ለሚሆኑ አፍቃሬ አሜሪካ ምሑራንና ባለሥልጣኖች በዩ.ኤስ.አይ.ኤስ በቤተ መጻሕፍቱ አዳራሽ ታየ። ይህ እንደሆነ ብ/ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ወሬውን ሰምተው ሥራ ቦታዬ ድረስ መጥተው «የቃኘው ሻለቃ በኮሪያ» የሚለውን ፊልም እንዴት ማየት እችላለሁ?" ብለው ጠየቁኝ። ፊልሙን ለማየት አሥር ደቂቃ ብቻ ስለሚወስድ እና ቢሮ□ም ምቹ ስለነበር ጥያቄአቸውን በአክብሮት ተቀብዬ አሳየኋቸው። በጣምም ●ደዱት። ፈገግ ብለው የብር አለሎ የመሰለ ዐይናቸውን ወዲያና ወዲህ አንከባለው እዩኝና መጀመሪያ «የክብር ዘበኛ ሠራዊት ሳያየው ሌላ ሰው እንዳያየው፣ እኔ ስፈ ች እልካለሁ፣ ሌላውን ሁሉ አንተ ፈጽም» ብለው ደስታ ባለበት ኮስተር ባለ ወታደራዊ

---

[12] *በተባሩት መንግሥታት ማኀበር የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ ሳሉ የሠሯቸውን ሥራዎች በተለይ የደቡብ ኮሪያ በሰሜን ኮሪያ ስትወረር ማኀበሩ ጥቃቷን ለመከላከል የአባል አገሮችን ጦር ትብብር ሲጠይቅ ኢትዮጵያ ያሳየችውን ፈጣንና ቁርጠኛ አቋም ሲያሳይ የኢትጵያን ቋሚ መልዕክተኛ ዘውዴ ገብረ ሕይወትን «ኖ ዴሊጌት ሐዝ ኤቨር ወርክድ አት ዘ ዩ ኤን ላይክ ሕይወት ኦቭ ኢትዮጵያ» እያለ ሲያደንቃቸው የሚታይበት ነው።*

ትዕዛዝ ቃና አዘውና አመሰግነውኝ ሔዱ። ከዚያም በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም. የሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት አዛ ሳለ በጄኔራሎች አድማ የተገደለው፣ የመቶ አለቃ (በኋላ ሜጀር ጄኔራል) ደምሴ ቡልቶና የሻምበል (በኋላ ኮሎኔል) እዮብ ገብረ ሚካኤልን ለክብር ዘበኛ ሠራዊት የሚያሳዩት የአሥራ ስድስት ሚሊሜትር የሲኒማ ፊልም ለመምረጥና ከነፕሮጀክተሩ ለመዋስ በጄኔራል መንግሥቱ ተልከው መጡ። የአያያዝ የአጠቃቀም ሥልጠናውን ከወሰዱ በኋላ የመረጧቸውን ፊልሞች ለሠራዊቱ ለማሳየት ወሰዱ።

ልክ እንዲሁ ከቤተ ክህነትም ሊቀጳጳስ በኋላ ፓትሪያሪክ አቡነ ቴዎፍሎስ፣ ከኢሣይያስ ዓለሜ (በኋላ ዶክተር)፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያናት በቅዳሴ መጨረሻና ከወንጌል ትምህርት በኋላ ለማሳረጊያ የሚጸለየውን ‹‹አባታችን ሆይ የምትኖር በሠማይ…›› የሚለውን ጸሎትና ዜማ ካወጣው ጋር ሆነው ሦስት ጊዜ ጎጃም ደብረ ኤሊያስ፣ ወስደውኝ ከላይ የተጠቀሱትን ፊልሞችና ሌሎች የልማትና የጤና ፊልሞች አሳይተናል። አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ የቅዱስ ደውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ዲን፣[13] ለትምህርት ቤቱ ፊልምና ፕሮጀክተር ተውሰው እየወሰዱ ከሚገለገሉት መኸል ነበሩ። የጠቅላይ ግዛቶችን በተመለከተም የሰሜኑን ጠቅላይ ግዛቶች ኤርትራን ጨምሮ፣ ከመሥሪያ ቤቱ ዳይሬክተር ከሚስተር አዲክ አንደርሰን ጋር በመሆን ከላይ የተጠቀሱትን ፊልሞች በጠቅላይ ግዛትና በአውራጃ ዋና ከተሞች እየዞርን አሳይተናል፡፡ የቀሩትን ጠቅላይ ግዛቶች ደግሞ በእኔ ኃላፊነት ዙሬ አሳይቼአለሁ።

ይህ ኃላፊነት በአገር ውስጥ ካሉት ብዙ የመንግሥት ባለሥልጣኖች፣ ከጠቅላይ ገዥዎች፣ እንደራሴዎችና ከአውራጃ ገዥዎች፣ ከፍተኛ የጦርና ፖሊስ አዛዦች ጋር ለመገናኘት፣ ለመተዋወቅና ለመቀራረብ አብቅቶኛል። ከላይ ከተጠቀሱት ተቋሞች ጀምሮ እስከ ቤተመንግሥት ድረስ እየተላኩ መጥተው አስጠርተው የሚያነጋግሩኝ ነበሩ፡፡ አልፎ አልፎ ሥራ ቦታ ድረስ ይመጡ ከነበሩት መካከል ልዑል መኮንን፣ ልዑል ሣህለ ሥላሴና ልዕልት እጅጋየሁን አስታውሳለሁ፡፡ በዚህ ዕድል በጣም ደስተኛ ነኝ፡፡ ለትምህርትና ሥራ የነበረኝ ፍቅር ለዚህ እንዳበቃኝ ሳስበውም ደስታዬ ዕጥፍ ይሆናል፡፡ መቼም የትምህርት ነገር ካነሳሁ ሥራ ላይም ሁኜ ጉጉቴ አለቀቀኝም፡፡ ይህን ጉጉቴን ያሳካልኛል ብዬ የምጠብቀው ተስፋም አድሮብኝ ነበር፡፡ እርሱም በስኮላር ሺፕ አሜሪካ እንሰድሀለን መባሌ ነበር፡፡ ዕድሌ ሆኖ ግን ወደ አሜሪካ እንድሔድ ሦስት ጊዜ ቢሞከርም፤ ይህ ነው በማልለው ምክንያት የትምህርት ሚኒስቴሩን የእስኮላር ሺፕ ክፍል ድጋፍ አጥቼ ተቋርጬ ቀረሁ፡፡ በዚያን ጊዜ ሰው የሌለው ሰው እጣ እንዲያ ነበር፡፡ በዚህ አድራጐት እያዘንኩ በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የኤክስቴንሽን ትምህርት በኢኮኖሚክስ ተመዝግቤ ትምህርቴን መከታተል ጀመርኩ፡፡ ያጋጣሚ ነገር ግን ከ፲፱፻፵፱ እስከ ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ

[13] በኋላ ሊቀ ሥልጣናት፣ የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳዳሪ እና በካቢኔ የመንፈሳዊ ጉዳይ ኃላፊ፣ ቀጥሎም አቡነ መልከጸዴቅ የተባሉት ሊቀጳጳስ (አሁን አሜሪካ በስደት የሚኖሩ)፤

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የኤክስቴንሽን ትምህርት በመከታተል ብቆይም አልፎ አልፎ *መሥሪያ* ቤቴ ለተለያዩ *ሥራዎች* ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ እየላከኝ በተደጋጋሚ የትምህርት ክፍለ ጊዜዎች ያመልጡኝ ነበር።

እስካሁን ከልጅነት ቡረቃ ወደ ትምህርት ቀጥሎ ደግሞ ወደሥራ ዓለም እንደተላለፍኩ አንስቼአለሁ። በትምህርቱ ላይ የፈጠረው ተፅዕኖ ባይኖረውም በመኻሉ በኑሮዬ የተከሰተ ታላቅ ለውጥ ነበር። ስለዚህ ይህን ለውጥ ወዳመጣው ወደ ጋብቻ የተሸጋገርኩበትን ሁኔታ ጥቂት ልበል። ጋብቻ የመሠረትኩት በ፲፱፻፵ ዓ.ም. ሲሆን፤ ዕድሜዬም ፳፯ ዓመት ነበር። ጋብቻዬ በአካባቢው የተለመደ ዓይነት ቢሆንም፤ የራሱ ለየት ያለ ታሪክም አለው። የወደፊት ሚስቴ የምትሆነው የትነበርሽና እኔ ሁለታችንም ጉንደር የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ነበርን። በወቅቱ ትምህርት ቤት የምንመጣው እሷ ከቅዳሜ ገበያ፣ እኔ ከቼቼላ ሲሆን፤ እንዳጋጣሚ ብዙ ጊዜ ከትምህርት ቤቱ አጥር መግቢያ በር እንገናኝ ነበር። አጋጣሚው ይገርመኝ ስለነበረ «አንቺ ልጅ ስታድጊ እኔ ነኝ የማገባሽ» እያልኩ እቀልድባት ነበር። እሷም አለመቀበሏን ወይም ተቃውሟዋን ለመግለጽ «ሪ፣ ኧ...ሪ!» እያለች ምራቋን እንትፍ እንትፍ እያለች ትሔድ ነበር።


ወላጆቼ ዕድሜያቸው የገፋ ስለነበር እኔ ትዳር ይዤ ሲያዩ የሚሰማቸወን ደስታ ሳያገኙ እንዳያልፉ በማሰብ በ፲፱፻፶ ዓ.ም. ሚስት ለማጨት ጉንደር ሔጄ ከተጠቆሙልኝ ሦስት ልጃገረዶች መኻል የትነበርሽ አንዷ ሆና አገኘኋት። ይህን ስረዳ በልጅነቷ ስለው የነበረው በእግዚአብሔር ፈቃድ እውን እንደሆነ አመንኩና አስፈላጊው ሁሉ ተሟልቶ በሕግ ተጋባን። እኔና ወ/ት የትነበርሽ (መቅደስ ቁምላቸው አጥሬ) ስድስት ልጆች አፍርተናል። ስምንት የልጅ ልጆችም ለመሳም በቅተናል። መቅደስ ቁምላቸው የእውቁ እግር ኳስ ተጫዋች የመንግሥቱ ወርቁ የቅርብ ዘመድ የባላምባራስ ቁምላቸው አጥሬ ልጅ ናት። የቀኛዝማች ወርቁ ስንቄ የባላምባራስ ቁምላቸው ቅርብ ዘመድ ናቸው። በአርበኝነቱም ሁለቱም በጀግንነታቸው የሚወደሱ ስለነበሩ በአለፋ ጣቁሳና በቋራ ከኢጣሊያ ጦር ጋር በነበረው የመጨረሻ የሞት ሽረት ውጊያ ከጠላት ጋር ሲፈጣረቁ ቀኛዝማች ወርቁ ስንቄ ቀደም ብለው በተመቱት ቁስል ህመም ባላምባራስ ቁምላቸው አጥሬ ደግሞ በውጊያው ዕለት በተመቱት ጥይት ቁስል ሁለቱም በአንድ ቀን ለአገርና ለወገን ክብር ተሰዉ።



*የእኔና የወይዘሪት መቅደስ የጋብቻ ፎቶ*



*ቤተሰቤ*



*ከሁለተኛ ባለቤቴ ከወይዘሮ ያልታዬ ወርቅ በላይ ጋር ተጋብተን ያፈራናት የምሥራች ብርሃኑ*

ከላይ እንደጠቀስኩት ትምህርቴን በሥራዬ ፀባይ ምክንያት ስልቶ መከታተል ቢያዳግተኝም፤ መማሬን አላቋረጥኩም ነበር። የትምህርቴ ነገር ግን ሥራዬ ላይ እክል ፈጠረ። ጉዳዩ እንዲህ ነው። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢኮኖሚክስ ኮርስ ስከታተል በዩኒቨርስቲው ለማጣቀሻ ከተቀመጡት መጻሕፍት የ"ዳስ ካፒታል" ሶሻሊስት ኢኮኖሚክ ሲስተም የሚለው መጽሐፍ የኮሌጁ ቤተ መጻሕፍት የነበረው አራት ቅጅ ብቻ ነበር። ይህ ደግሞ መጽሐፉን ለ፲፱፻፶፯ የቀንና ኤክስቴንሽን ተማሪ በውሰት ለማግኘት በጣም አስቸጋሪ ስላደረገው፤ እኔ ኤደን (ደቡብ የመን) ደርሶ የሚመጣ ሰው አግኝቼ ገዝቶ እንዲያመጣልኝ ጠይቄው፣ በ፲፱፻፶፮ ዓ.ም. አዲስ መጽሐፍ ገዝቶ አምጥቶልኝ ነበር። በወቅቱ የምሠራው የአሜሪካ ማስታወቂያ ክፍል (ዩ. ኤስ. አይ. ኤስ.) ቢሆንም በሥራ ቦታዬ ላይ ፋታ ሳገኝ ለማንበብ ከጽሕፈት ጠረጴዛዬ ላይ አስቀምጠው ነበር። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ መጽሐፉ ቢሮ ጠረጴዛዬ ላይ እንደተቀመጠ የመሥሪያ ቤቱ ዳይሬክተር ለሥራ ጉዳይ ፈልጎኝ ቢሮዬ ሲገባ ይህን መጽሐፍ ያይና በአንባቢነቱ ይደነቅ ነበርና ጠጋ ብሎ አርእስቱን ቢመለከት ‹‹ዳስ ካፒታል›› የሚል ሆኖ ያገኘዋል። ይሔኔ አድናቆቱን ለውጦ በምመራው ድርጅት ውስጥ ጊዜ ጠብቆ የሚፈነዳ ቦንብ እየተቀበረ ነው በሚል ይደነግጥና አሜሪካን ኤምባሲ ለነበሩ ማሪን ጋርዶች[14] አዛዥ ሁኔታውን በስልክ ይነግራል። ወዲያው ሁለት ጠርብ፣ ጠርብ የሚያክሉ ማሪን ጋርዶች የእጅ ማሠሪያ ካቴና፣ ረጃጅም የላስቲክ ዱላና ፎርቲ ፋይቭ ሽጉጥ ታጥቀው ተጣድፈው ወደ ቢሮዬ ገቡ። ሁኔታቸውን ያየ ሰው ትልቅ ወንጀል እንደተፈፀመ ሁሉ ግር ብሎ ከበበ። ከዚያ አንድ ጊዜ እጀን መጽሐፉ ላይ ጭኜ፣ ሁለተኛ በእጀ ይዤ፣ ሦስተኛ መጽሐፉ ጠረጴዛዬ ላይ እንዳለ እኔ ወንበሬ ላይ ተቀምጬ ፎቶግራፍ እንድነሳ ተደረገ። ይህን ተከትሎም ድርጊቱ ለሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ መሥሪያ ቤት በስልክ ተነግሮ ሁለት የፀጥታ መሥሪያ ቤት ሰዎች መጡና አስፈላጊ ነው ያሉትን ማስታወሻ ይዘው ፎቶግራፍም አንስተው ሳያሥሩ ወደ ፀጥታ መሥሪያ ቤት እንሒድ ብለው ወሰዱኝ። እዚያም ቃሌን ሲጠይቁኝ ያ መጽሐፍ በእጄ ሊገባ የቻለበት ምክንያት ምን እንደሆነ ከላይ የገለጽኩትን ስደግምላቸው፤ ከሻለቃ ወርቅነህ ዘንድ አቀረቡኝ።

ከሻለቃ ወርቅነህ ጋር ከዚያ በፊት ሁለት ሦስት ጊዜ አትላንቲክ ሆቴል (ቀድሞ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጉዳና ይባል በነበረው መንገድ ወደ ራስ መኰንን ድልድይ በሚወስደው ጉዳና ብሪቲሽ ካውንስል ከነበረበት አጠገብ የነበረ) በምሣ ጊዜ ተገናኝተናል። ያስተዋወቀንም አብሮ አደግ ጓደኛው የሻለቃ እምሩ ወንዴ ነበር። የሻለቃ ወርቅነህ ነገርን አክብዶና ፊቱን ቋጥሮ አይናገርም። ስቀርብ ፈገግ ብሎ ከመቀመጫው ብድግ በማለት ሰላምታ ሰጠኝና አሁንም ፈገግ እንዳለ ከመርማሪዎቹ ስለኔ የሰማውን መቀበሉንና ምንም የሚያሳስብ ነገር አለመኖሩን ገልጾ ምሣ ለመብላት


[14] ማሪን ጋዶች አጠቃላይ የአሜሪካንን ጥቅም የሚጠብቁ የፀጥታ ጠባቂዎች ናቸው።

እንገናኝበት ከነበረው ሆቴል ምግብ እንዲያስመጡልኝ መርማሪዎቹን አዞ አንድ ብር ተኩል ወጭ ሆኖ ምሣ መጣልኝ። ነገሩን አጣጥዬ ባየውም ምግቡ አልበላኝ አለ።

ለማንኛውም በማግሥቱ ፀጥታ መሥሪያ ቤቱ የተያዝኩበት ድርጊት ከኮምኒስት ሥርዓት ስርጸት ጋር ፈጽሞ ያላቆራኘኝ መሆኑን ለአሜሪካኖቹ ገለጸ። አሜሪካኖቹ ግን ለሦስት ቀን ያህል ከእነርሱው ዘንድ አቆይተውኝ እንዲያጣሩ በመጠየቃቸው ይኸው ተነገረኝ። በአራተኛው ቀን ለማጣራት ተጨማሪ ስምንት ቀናት እንድቆይ ሌላ ጥያቄ ስለቀረበ፤ ቆየሁ። ስምንቱን ቀናት ስጨርስም፤ ደሞዙን እንከፍላለን፣ ለአንድ ወር ከእናንተ ጋር ይቆይ የሚል እንደገና ሌላ ጥያቄ መጣና ቆየሁ። በዚህ ቆይታዬ ግን የሻለቃ ወርቅነህ ቤተ መጻሕፍት ብታቋቁምልን ብሎ ጠየቀኝና እሺ ብዬ መጻሕፍቱን፣ የተለያዩ ጋዜጦችን፣ መጽሔቶችን ለማግኘትና ለማንበብ በሚያመች ሁኔታ አደራጅቼ ዓይቶት ወደደው። እንደገና አሜሪካኖቹ «ሁለተኛ ወርም ከዚያው ቢቆይ» ሲሉት «አይ ይህን አላደርግም» ብሎ ከመለሰላቸው በኋላ እኔን «ለፈረንጅ ከምታገለግል ለምን ለአገርህ አታገለግልም» በማለት ጠየቀኝ። እኔም ቁጭት ላይ ስለነበርኩ ለማገልገል ፈቃደኛ መሆኔን ወዲያው ገልጨ እዚያው የሻለቃ ወርቅነህ ከሚመራው የሕዝብ ፀጥታ መምሪያ መሥሪያ ቤት ተቀጥሬ ሥራ ጀመርኩ።

# ምዕራፍ ፪
# ቅድመ ሁኔታ
## ተፈሪ መኮንን[1]

ተፈሪ ከራስ መኮንንና ከወይዘሮ የሺመቤት ጋምጮ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፰፻፹፬ ዓ.ም. በሐረርጌ ግዛት ኤጀርሳ ጉሮ ተወለዱ። የአባታቸው እናት ወ/ሮ ተናኘ ወርቅ፣ የንጉሥ ሣኅለ ሥላሴ ልጅ ሲሆኑ፤ የአባታቸው አባት ደግሞ የደባና የመንዝ ባላባት ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ጉዲሳ ናቸው። የእናታቸው እናት ወ/ሮ ወለተ ጊዮርጊስ የጉራጌ ባላባት ናቸው ሲባል ኑሯል። ወ/ሮ የሺመቤት በአባታቸው የወረኢሉ ባላባት የሼህ ዓሊዬ ኪቶ (የኦሮሞ እስላም) የልጅ ልጅ የሼህ ዓሊዬ ጋምጮ ልጅ ናቸው።[2] አቶ ብርሃኑ ድንቄ "አጭር የኢትዮጵያ ታሪክ" በተባለው መጽሐፋቸው "የሺመቤት ጌታቸው" ከሚሉት ጋር አይመሳሰልም። አምባሳደር ዘውዴ ረታም ወ/ሮ ወለተ ጊዮርጊስ የመንዝና የተጉለት ባላባት እንጂ የጉራጌ ተወላጅ አይደሉም ሲሉ ገልጸዋል። የወ/ሮ የሺመቤት ዘመዶች ግን የአቶ ብርሃኑ ድንቄን ገለጻ አይቀበሉትም። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ስለዚህ ሁኔታ በሌላ የታሪክ መጽሐፍ የተገለጸ ባይኖርም፤ አቶ በሪሁን ከበደ የሺመቤት ጋምቾ[3] ሲሉ የሚጠቅሱት ከዚህ ጋር የሚሔድ ነው። ዐፄ ኃይለ




*ልጅ ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ*

---

[1] *ይህ ምዕራፍ ስለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትውልድና የንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሥልጣን አመጣጥ በጥቂቱ የሚያስታውስ ሲሆን፤ ዓላማው የጽሑፉ ዋና ታሪክ የሆነውን የ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ እንዲካሔድ መነሻ የሆኑ ሁኔታዎች እንዴት እንደተፈጠሩና ተባብሰው እመጨረሻው ደረጃ መድረስ እንዴት እንደቻሉ አስቀድሞ አጠር አድርጎ ለማመልከት ነው። ይህ እንግዲህ ሙከራው እንደ ደራሽ ውሀ በድንገት የተከሰተ እና መሪዎቹም በግብታዊነት የተነሡ አለመሆኑን ለማስገንዘብ ይረዳል ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ስለ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ እኔ የዚህ ታሪክ ጸሐፊ ባገኘሁት መረጃ ተመርኩዤ የጠቀስኩት ነጥብ፣ ከዚህ ቀደም በተጻፉ የታሪክ መጻሕፍት ውስጥ ተካተው የማያውቁና ወደፊት በዚህ ጉዳይ ላይ ምርምር ለሚያደርጉ ጸሐፊዎች በመነሻነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ይሆናል በሚል እምነት ጭምር ነው።*

[2] *የወ/ሮ የሺመቤት በአባታቸው በኩል ያለው የዘር ሀረግ መረጃ የተገኘው የወ/ሮ የሺመቤት የቅርብ ዘመድ ከሆኑት ከአርቲስት ቻቺ ታደሰ አባት ከልጅ ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ ቤተዘመድ ነው። ልጅ ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ ከንጉሡ ጋር የነበራቸው ዝምድና ጥብቅነት ማሳያ ከሚባሉት ነገሮች አንዱ በማይጨው ጦርነት መፈታት ሲፈጠር፤ በተለመደው በደሴ መንገድ ወደአዲስ አበባ መመለስ ሲገባ የልጅ እያሱ ወገኖች አደጋ ይጥላሉ ተብሎ ስለተሰጋ መንገዱ በደሴ መሆኑ ቀርቶ በተንታ በኩል እንዲሆን የመከሩና ከፊት ቀድመው መንገዱን መርምረው ንጉሡን የወሰዱ ስለመሆናቸው መነገሩ ነው።*

[3] *በሪሁን ከበደ፣ **የዓፄ ኃይለ ሥላሴ ታሪክ**፣ ገጽ ፻፷፩*



ልጅ ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ

ሥላሴም ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ በተባለው በመጀመሪያው መጽሐፋቸው ስለእናታቸው አባት ያነሡት ነገር የለም፡፡ አንድም ጊዜ «አማራ ነኝ፣ ኦሮሞ ነኝ፣ ትግሬ ነኝ ወይም ጉራጌ ነኝ» ብለው አያውቁም፡፡ ከዚህም ለመውጣት የትውልድ ጉዳይ ሲነሣ «ከንጉሥ ሰሎሞን ከተገኘው ከቀዳማዊ ምኒልክ ነው» በማለት የትውልድ ሐረጋቸውን ጥያቄ ይዘጋሉ፡፡

እናታቸው «የሾተላይ ሰለባ»[4] ስለነበሩ፤ ተፈሪ እንደተወለዱ በቆየው የአገር ልማድና ዕምነት መሠረት እናታቸው ልጃቸውን ሳያዩዋቸው የተገላገሉበት ቤት ግድግዳ ተቀዶ ሕጻኑን በማውጣት ሌላ ዘመድ ሕፃን ተፈሪን እንዲወስድ ተደረገ፡፡ ከጥቂት ወራት በኋላ ለአባታቸው እህት ልጅ ለወ/ሮ መዝለቂያ ተሰጥተው ከልጃቸው ከእምሩ ኃይለ ሥላሴ (በኋላ ልዑል ራስ) ጋር እንደ መንትያ የአንድ እናት ጡት ለሁለት እየጠቡ በአንድነት አደጉ፡፡ ወ/ሮ የሺመቤት ልጃቸውን ሳያዩ በወለዱ በሁለት ዓመታቸው በ፲፰፻፹፮ ዓ.ም. የተፈሪን ተከታይ ሲወልዱ በወሊድ በመሞታቸው ተፈሪ የእናት ፍቅር ሳያገኙ ማደግ ዕጣቸው ሆነ፡፡ እነዚህ እንደመንትያ የሚታዩ ልጆች ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ፣ ራስ መኮንን ባቋቋሙት ሆስፒታል ይሠሩ የነበሩት ፈረንሳዊው ዶ/ር ቪታሊያ እና አባ ሣሙኤል የተባሉ ኢትዮጵያዊ የካቶሊክ ሚሲዮን መምህር የፈረንሳይኛ ቋንቋ በትጋትና በጥንቃቄ አስተማሯቸው፡፡ በአማርኛ ትምህርትና በጥሩ ሥነ ምግባርም ተኮትኩተው እንዲያድጉ በአደሬ ጢቆ ቅድስት ሥላሴ ትምህርት ቤት አስገቧቸው፡፡

ተፈሪ በዚያ የሕፃንነት ዕድሜያቸው እናታቸውን ማግኘት አለመቻላቸውና በተለይ በአስተዋይነታቸውና በቁምነገረኛነታቸው የሚወዱዋቸውና የሚያከብሯቸው አባታቸው አዘውትረው በሥራ ምክንያት ወደውጭ እየጣሏቸው በመሔዳቸው፤ ብቸኝነቱ፣ ቅሬታና ሐዘን ሳይፈጥርባቸው አልቀረም፡፡ ይህን ክፍተት ለመሸፈንም አያታቸው ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ፣ ተፈሪ በሚገኙበት በቤትና በአስተዳደር ሥራ እየገቡ ብዙ የአሠራርና የአስተሳሰብ መንገድ ሳያስይዙ አልቀሩም ይባላል፡፡ ዐፄ ምኒልክ ከአሽከሩ (ልጁ) ካሣ (በኋላ ዐፄ ዮሐንስ) እና ከመሸሻ ቴዎድሮስ (በኋላ ራስ) እና ከዓለማየሁ ቴዎድሮስ ጋር (በዕድሜ አቻ ባይሆኑም) በዐፄ ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት አብረው ሲያድጉ፤ ቴዎድሮስ ከውጭ ከመጡ የውጭ ዜጎች ጋር ያደርጉ በነበረው ግንኙነት ስለሰሙት የአውሮፓ ሥልጣኔ በአዕምሮአቸው ተቀርጾና ትልቅ ክበሬታ አሳድሮባቸው አደጉ፡፡ ስለዚህ እሳቸው ወደ ሥልጣን ሲመጡ ባገኙት ተጨማሪ የአውሮፓ የሥልጣኔ ዕድገት ዜና ተመስጠው ኢትዮጵያን ከነበረችበት ጉልታዊ ሥርዓት በማውጣት ወደ ዘመናዊ አስተዳደር ለማሸጋገር የሚያደርጉትን ጥረት ለማሳካት እንዲረዱዋቸው እንደራሴዎችን ይልኩ ነበር፡፡ ከእነዚህ ወደ አውሮፓ ከሚልኳቸው መኳንንት መካከል አንዱ ራስ መኮንን ነበሩ፡፡ ራስ መኮንን በአውሮፓ ያዩትን ሁሉ ለንጉሡ በዝርዝር ያቀርቡ ነበር፡፡ ለልጃቸው ለተፈሪም ከዚያ ባላነሰ


[4] ሾተላይ፤ በእናትና ልጅ ደም አለመስማማት ሕፃናት በወሊድ የሚጠፉበት ሁኔታ ነው፡፡

ሁኔታ በማስረዳት ከሁለቱ የፈረንሳይ ቋንቋ መምህራን ባገኙት ዕውቀትና ሐሳብ ላይ ማጠናከሪያ ምክር እየሰጡ ልጃቸውን ለወደፊት የሥልጣን ዕድገት ያመቻቹዋቸው ነበር።

## የሥልጣን ፉክክር

ራስ መኮንን ልጃቸው ቀስ በቀስ ወደ ሥልጣን እንዲወጡ በነበራቸው ጽኑ ፍላጎት የተነሣ፣ ተፈሪ ዕድሜያቸው ፲፬ ዓመት ሲሆን ጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ.ም. ደጃዝማች ብለው የኃረ ሙለታ አውራጃ ገዥ አድርገው ሾሟቸው።






ልጅ ኢያሱ ሚካኤል

ደጃዝማች ተፈሪ መኮንን



ደጃዝማች ተፈሪ መኮንን



ልጅ ኢያሱ ሚካኤል



*እቴጌ ጣይቱ ብጡል*

ተፈሪ በመጀመሪያው መጽሐፋቸው እንደጠቀሱት፣ ራስ መኮንን መጋቢት ፲፫ ቀን ፲፰፻፹፰ ዓ.ም. ስላረፉ፤ ዐፄ ምኒልክ በቤተ መንግሥታቸው የሐዘን ውሎ እንዲደረግ በመወሰን ልጃቸው ደጃዝማች ተፈሪን ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ አደረጉ። የሐዘን ጊዜው ሲያበቃ የደጃዝማች ተፈሪ መኳንንትና ሠራዊት የአባታቸውን ግዛት ሐረርጌን ይሰጡአቸዋል የሚል ግምት ይዘው ቢነሱም፤ ዐፄ ምኒልክ ሐረርጌን ራስ መኮንን ከወይዘሮ አሰለፈች ወልደሐና የደጃዝማች ገሠሠ እህት ከልዕልት የሻሸወርቅ እናት ለወለዱአቸው ለደጃዝማች ይልማ በመስጠታቸው፤ ደጃዝማች ተፈሪ የሥልጣን ፉክክሩን "ሀ" ብለው ጀመሩ። ሆኖም ደጃዝማች ተፈሪ የሆዳቸውን በሆዳቸው አድርገው ግዛታቸውን በእንደራሴ እያስተዳደሩ አዲስ አበባ በመቀመጥ ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርታቸውን ቀጠሉ። ደጃዝማች ተፈሪ አዲስ አበባ እንዳሉ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ሕመም መሻሻል ባለማሳየቱና አልጋወራሽ መሰየሙ ግድ ስለሆነ፤ ዳግማዊ ምኒልክ ልጃቸው ወ/ሮ ሸዋረጋ ምኒልክ ከሁለተኛው ባላቸው[5] ከንጉሥ ሚካኤል የወለዷቸው ልጅ ኢያሱን በራስ ተሰማ ሞግዚትነትና እንደራሴነት አልጋወራሽ ሆነው እንዲያስተዳድሩ ሰየሙ።

---

5 *የመጀመሪያው ደጃዝማች ወዳጆ ጎበና ነበሩ*



የልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽነት በዐዋጅ ቢነገርም፤ የመንግሥቱ ሥልጣን በእቴጌ ጣይቱ ብጡል እጅ መቆየት ያላስደሰታቸው መኳንንት፣ በተለይ ራስ ተሰማ እቴጌ ጣይቱን ከሥልጣን ለማውረድ መኳንንቱን ሲያሳድሙ፤ ተፈሪ ሐሳቡን ባይጠሉትም ትብብራቸውን ከበስተጀርባ እንጂ ፊት ለፊት እንዳላደረጉ ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ይገልጻሉ። እቴጌም፣ ይህን እንደ ውለታ ቆጥረው የካቲት ፳፬ ቀን ፲፱፻፪ ዓ.ም. የአባታቸው የግዛት አገር የነበረውን ሐረርጌን በግዛትነት ሰጧቸው። ይህም የመጨረሻው የእቴጌ ጣይቱ ሥልጣን ውሳኔ ሆነ።

ሆኖም የደጃዝማች ተፈሪ ወደ ሐረርጌ መሔድ እንዲዘገይ ተደርጐ በልጅ ኢያሱና በእርሳቸው መካከል መቀናቀን እንዳይኖር ለማድረግ ራስ ተሰማ ደጃዝማች ተፈሪን ወደ አቡነ ማቴዎስ ቤት በመውሰድ ታማኝነታቸውን በመሐላ እንዲያፀድቁ ካደረጉ በኋላ ወደ ግዛታቸው እንዲሔዱ ተፈቀደ። ደጃዝማች ተፈሪ ሐረርጌን ለአንድ ዓመት ያህል በመልካም ሁኔታ እያስተዳደሩ እንዳሉ፣ ቀደም ሲል ለመተማመኑ የተደረገው መሐላ ብቻ እንደማይበቃና በዝምድናም እሥር ማጠናከር እንደሚያስፈልግ በማመን፣ ልጅ ኢያሱ የእህታቸውን የወይዘሮ ስኂን ሚካኤልን ልጅ፣ ወይዘሮ መነንን ከደጃዝማች ተፈሪ ጋር ለማጋባት ወሰኑ። ሐሳባቸውን ለመፈፀም ባለቤታቸውን ራስ ልዑል ሰገድን ሸዋ ጊሚራ ልከው በመቻ ሥራ ላይ ባሉበት ጊዜ፣ ቀኛዝማች እምሩ ኃይለ ሥላሴ (በኋላ ልዑል ራስ) አድራሽነት ወ/ሮ መነንን በሚስትነት ሲልኩላቸው ደጃዝማች ተፈሪም ቁልቢ ድረስ በመምጣት ተቀብለው ሐምሌ ፲፫ ቀን ፲፱፻፫ ዓ.ም. ዕድሜያቸው ፲፱ ዓመት ሊሞላ ሲል ጋብቻቸውን ፈፀሙ።


እቴጌ መነን

ልጅ ኢያሱ ኃይላቸውን እያጠናከሩ ሳሉ ዐፄ ኢያሱ ፫ኛ ተብለው እንዲነግሡ ተደጋግሞ ቢጠየቁ "አባቴ ባቀኑት አገር ላይ ምንም ሳልጨምር ምን ሠርቻለሁ ብዬ ነው የምነግሠው?" ይሉ እንደነበር ይወሳል። ይህም የልጅ ኢያሱ የግዛት ማስፋፋት ዕቅድ ከፍ ያለ እንደ ነበር ያመለክታል። በኢትዮጵያ ወሰን አካባቢ በነበሩ የቅኝ ገዥዎች የኢትዮጵያ ድንበር ይጣሳል የሚል ሥጋት ስለነበርና የግዛት ማስፋፋት ዕቅዳቸውን ከግብ ለማድረስ፣ ልጅ ኢያሱ የወቅቱ ኃያል መንግሥት ከነበረው ከጀርመን ጋር ወዳጅነት ጀመሩ። ሐሳቡ ጀርመን ከኢትዮጵያ ጋር የሚዋሰን የቅኝ



እቴጌ መነን

ግዛት ካላቸው ከእንግሊዝ፣ ከጣሊያንና ከፈረንሳይ ጋር ጦርነት ብታደርግና ብታሸንፍ ኢትዮጵያ የጀርመን ተባባሪ በመሆኗ ከተሸናፊዎች የሚለቀቀውን አገር ወደራሷ ግዛት ለማጠቃለል ይረዳታል የሚል ነው:: የዚህ ውጥን መነሻ ጀርመን አገር ያደጉት የልጅ ኢያሱ ደጋፊ የነበሩት የነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ምክር ነው ይባላል:: ልጅ ኢያሱ በዚህ መልኩ ከጀርመን መንግሥት ጋር የመሠረቱት ወዳጅነት የተጠቀሱትን ሦስት የአውራብች አገር ቅኝ ገዥዎች ያሳስባቸዋል:: በተለይ ልጅ ኢያሱ የእንግሊዝ ሱማሌን የጐሳ መሪ ሼኽ አብዱላሂ ሁሴንን በመሣሪያ እያጠናከሩ የሞራል ድጋፍ መስጠታቸው እነዚህን አገራት ከጀርባ ሊያስጠቃን ይችላል የሚል ሥጋት ውስጥ ከቷቸዋል:: ይህም ልጅ ኢያሱን ከመንግሥት ሥልጣን ለማውረድ አቋም እንዲይዙ በማድረጉ፤ በወቅቱ ሥልጣንና ተሰሚነት ለነበራቸው ለፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ልጅ ኢያሱን ከሥልጣን እንዲያወርዱ ካላወረዱ ግን እንደሚወጓቸው ማስጠንቀቂያ ስለመስጠታቸውና ኢያሱን ከዙፋን ለማውረድ ለሚያስፈልገው እንቅስቃሴ የሥራ ማስኬጃ እያንዳንዳቸው አንድ አንድ መቶ ሺህ የጠገራ (የማርያተሬዛ) ብር አዋጥተው ለመስጠት ስለመዋዋላቸውም በሰፊው ተወርቶ ነበር::

በሌላ በኩል ደጃዝማች ተፈሪ የልጅ ኢያሱን ድጋፍ ለመሸርሸር እንቅስቃሴ ያደርጉ ነበር:: ከነዚህ መካከል አንዱ ከውስጥ የመኳንንቱን ድጋፍ በእጅ መንሻና በስጦታ ወደራሳቸው ለማዞር ያደረጉት ጥረት ነው:: ሌላው ልጅ ኢያሱን የድጋፍ መሠረት ለማሳጣት ወጪውን የእንግሊዝ ኤምባሲ የቻለው የተባለው በፎቶግራፍ ማገጣጠም ቴክኒክ የተዘጋጀው ፎቶ ነው:: ይህ ቴክኒክ በሥራ ላይ የዋለው በወቅቱ ታዋቂ የንጉሥ ሚካኤልና የልጅ ኢያሱ ፎቶግራፍ አንሺ የነበሩት ሙሴ ሊዮን ያዘጂያን[6] አዳል ውስጥ ልጅ ኢያሱን በእስላም ባሕላዊ አለባበስ ግልድም አገልድመው አንስተዋቸው የነበረውን ፎቶግራፍ ከዐፄ ምኒልክና ከእቴጌ ጣይቱ ፎቶግራፍ አንሺ ከነበሩት ከሙሴ ጴጥሮስ ቦያጅያን[7] ጋር በመሆን፣ ግልድም አገልድመው በተነሡት ፎቶግራፍ ላይ ካይሮ ሔደው በፎቶ ሞንታዥ[8] ከእስላም ጥምጥም ፎቶግራፍ ጋር በማገጣጠም አሠርተው ሦስት ሺህ የፎቶግራፍ ቅጅ በማስመጣት በየአገሩ ላሉ መኳንንትና ለልጅ ኢያሱ አባት ለንጉሥ ሚካኤል ጭምር በመሸኛ ደብዳቤ ተሰራጭቷል:: ይህ መረጃ ተክለ ጻድቅን ጨምሮ በሌሎች የውስጥም ጸሐፊዎችም ሆነ የውጭ ጸሐፊዎች ይደገፋል:: መሳፍንቱና መኳንንቱ ይህን ካየ በኋላ «ሃይማኖቱን ከለወጠማ የምኒልክን አደራ አልበላንም፤ አደራ አላፈረስንም» እያለ እንዲደፋፈር ስላደረገው መክዳት ስለጀመረ፤ ልጅ ኢያሱን ደጋፊ በማሳጣት ብቻቸውን (መለመላቸውን) አስቀራቸው:: በዚህ

---


[6] የሲኒማ አምፔር ባለቤት የነበሩት የሙሴ ፓይላክ አባት ናቸው::

[7] በአዲስ አበባ የታወቁ የቤተ መንግሥትና የሕዝብ ፎቶግራፍ አንሺ የነበሩት የሙሴ ቶኒ አባት ናቸው::

[8] የሞንታዥ ፎቶ ግራፍ ጥበብ ሁለት የተለያዩ ፎቶግራፎችን በጥንቃቄ በማዋሃድ አንድ ፎቶግራፍ እንዲመስሉ ማድረግ ነው:: ይህን መረጃ ያረጋገጥኩት በ፲፱፻፷፪ ዓ. ም. አዲስ አበባ ሐግቤስ ኩባንያ አሠራ በነበረበት ጊዜ አብረውኝ ይሠሩ ለነበሩ ኢትዮጵያውያን የአርመን ተወላጆች ታሪኩን አንስቶ ስንጨዋወት የፎቶግራፍ አንሺዎቹ ዘመዶች አሁን ደጃች ውቤ ሠፈር አሉ ብለው ወስደው አገናኝተውኝ ይህ ታሪክ እውነት መሆኑን አረጋግጠውልኛል::

ዓይነት ኢያሱን ከሥልጣን የማውረዱ ዘመቻ በየመልኩ ሲካሔድ ቆይቶ መስከረም ፲፯ ቀን ፲፱፻፱ ዓ.ም. ልጅ ኢያሱ ከሥልጣን እንዲወርዱ፣ ወ/ሮ ዘውዲቱ ምኒልክና ደጃዝማች ተፈሪ ወደ ሥልጣን እንዲወጡ ተደረገ። ሁኔታውን በወቅቱ የታዘበው የኢትዮጵያ ሕዝብ በፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ላይ ቅሬታ አሰማ። በዚህም ደጃዝማች ተፈሪ ምኞታቸው ተሳክቶ፣ የሥልጣን መወጣጫ እርካቡን ተቆናጠጡ። ከዚህ በኋላ ያለው ወይም የሚመጣው ተቀናቃኝ ሁሉ ከቁጥር እንደማይገባና ከዐላማቸው ሊያግዳቸው እንደማይችል ተማመኑ።

ተፈሪ ራስና አልጋ ወራሽ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያን አውሮፓውያን በሥልጣኔ ከደረሱበት ደረጃ ለማድረስ ወደሚያስችለው ሒደት ለማስገባት ፍላጎትና ጉጉት አደረባቸው። ይሁን እንጂ ይህን ሐሳብ የሚደግፍና የሚያራምድ አጋዥ በቂ የተማረ የሰው ኃይል በሌለበት፣ የቆየውን ልማድ በያዙ ከምኒልክና ከኢያሱ በተላለፉ በታላላቅ መሳፍንትና መኳንንት በተያዘ መንግሥት የአስተዳደር ሚዛኑን ጠብቆ በአዲስ የሥልጣኔ መንገድ ለመምራት ቀላል አልሆነላቸውም። ቢሆንም "ደፋርና ጢስ መውጫ አያጣም" እንዲሉ ተፈሪ የአገር አስተዳደሩን ሥራ ኃላፊነት በተማሩና ራዕይ ባላቸው ሰዎች ለመተካት ብዙ ጥረት ያደርጉ ነበር። ይህንን የለውጥ እርምጃ ለማሳካት ስለወሰዷቸው እርምጃዎች በዘመኑ የነበሩ ሰዎች የዓይን ምስክርነት ሰጥተዋል። ከነዚህ መካከል ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት አንዱ ናቸው።[9] ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት በጻፉት ግለ ታሪካቸው ስለሰውጡ ውጥን አጀማመር ይህን ይላሉ።



ንግሥት ዘውዲቱ

> ከሂርና ተጠርቼ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ። አልጋ ወራሽም በልጅ ኢያሱ ጊዜ ስላገር አስተዳደር የጻፍከውን ደንብ ስጠኝና ልመርምረው" አሉኝና ሰጠኋቸው። ከዚያም "የጻፍከውን ደንብ በጨርጨር ላይ መሞከር ይቻላል። በጨርጨር ከተሞከረ በኋላ በሌሎቹም አውራጃዎች ልናገባው እንችላለን" አሉ አልጋ ወራሽ ተፈሪ።

---

[9] ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያትመጀመሪያ የልጅ ኢያሱ ኋላ የራስና አልጋ ወራሽ ተፈሪ አማካሪና ደጋፊ ነበሩ።



*ንግሥት ዘውዲቱ*

አሁን እንደዚህ! እንደዚህ! ይላሉ በኋላ መሰናክል ያደርጉብኛል፣ ይቅርብኝ" አልኳቸው:: "ምንም መሰናክል አላደርግብህም፣ ደንቡን ፈርሜ ማኅተም ተደርጐበት እሰጥሃለሁ:: ከዚያ በኋላ በደንቡ ብቻ ትፈጽማለህ፣ ማንም አይደርስብህም" አሉኝ አልጋወራሹ:: እኔ ከዚህ ይበልጥ የሚወደድ ሥራ አላገኝም:: ያገር አስተዳደር ሞዴል በጨርጨር ላይ አሳይቼ፣ ከዚያ በኋላ የሕዝቡ ትዳር ሲደረጅ፣ የመንግሥቱ ገቢ ሲበረክት፣ ሽፍታና ወስላታ ሲጠፋ፣ ሥራው የሚመሠረተው በትክክለኛ ፕሪንሲፕ (ዕላማ) ላይ ሲሆን፣ ሰው ሁሉ እየሠራ መጠቀም ሲችል፣ ለራሱ መመከቱን አይተውም [መብቱን ማስከበሩ ማለታቸው ነው] ብዬ ሥራውን ጀመርኩ::

አሁን ያለው የጨርጨር ዋና ከተማ "ቁኒ" ለከተማነት የማይስማማ መስሎ ስለታየኝ "ጭሮን" ሔጄ አየሁት:: ቦታው ለዋና ከተማነት የሚስማማ በቂ ውሀ፣ ለቤት መሥሪያ የሚሆን ድንጋይና እንጨትም አለው:: ስለዚህ፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን በመልክ፣ በመልኩ ከደለደልኩ በኋላ ቀሪውን መሬት ደግሞ ለሕዝብ እንዲሠራ አደረኩ:: የጭሮ ከተማ በሁለት ወር ተሠርቶ አለቀ:: ውብ ከተማ ተሠራ ተብሎ ወሬው በየአገሩ ተዳረሰ፤ ፈረንጆች እየመጡ ጐበኙት:: የዚህን ሁሉ ድልድል ለአልጋ ወራሽ ላኩላቸውና ዋና ዋናቹን ሹሞች እሳቸው ሾሙ:: የወረዳዎችንና ሌሎች ሹሞችን እኔ ሾምኩ:: ለየወረዳው ሠራተኞች ፖስታ በየሣምንቱ እንዲመላለስ ተደረገ:: የሥራ መከናወን ተጀመረ:: ከዚህ በኋላ በያመቱ የሚከናወነው ሥራ እየተሰናዳ (ፕሮግራም እየወጣለት) ይፈጸም ጀመር::

የፍርድ ሥራ እንዲፋጠን ታዛቢዎችና የክስ ዳኛ (ዐቃቤ ሕግ) በተለየ ተደረጉ::

የክስ ዳኛ ባላጋራዎችን አቅርቦ ቃላቸውን እያስጣፈ ያስፈርማል:: ወንበሮች ቃሉን አስነብበውና መርምረው ይፈርዳሉ:: ታዛቢዎች አጣጥፈው ፍርዱ በሦስት ቀኖች ውስጥ በጥፈት ተመስክሮ እንዲሰጥ ግዴታ ሆኗል:: አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን ይህን ሁሉ ከሰሙ በኋላ "የቆረቆርከውን ከተማ ማን ብለህ ትሰይመዋለህ?" ብለው በጥፈት ጠየቁኝ:: እኔም "በጥንት ስሙ ጭሮ እለዋለሁ" ስል መለስኩላቸው:: "አሰበ ተፈሪ ብለህ ሰይመው" ብለው ጣፉልኝ:: "በቁምዎ ለራስዎ ስያሜ ከማውጣት ሕዝብ በኋላ መታሰቢያ ብሎ አውቆ በስምዎ ቢሰይመው ይሻላል" ስል ጣፍኩላቸው::

"እኛ እንዳልነህ አድርግ" ሲሉ በመቆየም ዓይነት ጣፉልኝ:: እኔም "ምን ቸገረኝ" ብዬ ተቀበልኩኝ::


የጨርጨር መሬት ሁሉ በርስትነት ታደለ:: የቁርጥ ግምት ግብር ከዳር እስከዳር ተደለደለ:: በጨርጨር ሥራ ስገባ በቁኒ ግምጃ ቤት የተገኘው ገንዘብ ስድስት መቶ ትሙን ሃምሣ ሻማ ነበር:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ገቢና ወጭ በየቀኑ እየታሰበ በጥፈት ይቀርብልኛል:: ያመት ገቢያችን ከሁለት መቶ ሺህ (ጠገራ) ብር በልጧል:: ገቢያችን እየበዛ እንዲሔድ ማድረግ ያስፈልጋል:: የመልከኛ ማደሪያ ሁሉ ሌላውም በትርፍነት ታውቆ የተቀመጠው መሬት ሁሉ እየተሸጠ ወይም ለድርጉኛ እየተሰጠ እንዲገብርበት አደረግሁ:: በመሬት ሽያጭና በግብር የምናገኘው ገንዘብ ገቢያችንን ከፍ አደረገልን::

## እንደ ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት አገላለጽ ሕዝቡ

> ... ጭቅጭቅ ስለቀረለት ጊዜ ተቆጥቦለት፣ ጉልበቱን ለሥራ ማከናወኛ ስላአደረገውና ገቢው ስላመቸው ትዳሩ መደርጀት ጀመረ። የመሬት ግብር በቁርጥ አደር ስለተደረገ ባለርስቱ የሚገብረው በዕዳሪውም፣ በጨፌውም፣ በጫካውም፣ ባፈሩም፣ በድንጋዩም መሆኑ ነውና ማንም ሰው ከባለመሬቱ ሳያስፈቅድ ምንም እንዳይቆርጥ እንዳያጭድ ባዋጅ ተከለከለ። በሕዝብ ታውቆ ከሕዝብ የተሰበሰበ ገንዘብ ተመልሶ ለሕዝብ ልማትና አገልግሎት በማዋል ያውራጃ የራስ ገዝ ምሳሌ ሆኖ ታዬ። መሬቱ የሚያፈራለት ሁሉ ዋጋ አገኘ የጨርጨር ኑሮ ጤነኛ ሆነ። በየቤቱ ሁሉም በሳህን መብላት ጀመረ።
>
> ሴቶች ጥልፍ ቀሚስና ኩታ፣ ወንዶች ኮትና ሱሪ በርኖስ መልበስ ጀመሩ። ሥራዬን ጠንቅቄ ሌትም ቀንም ሳላርፍ በመሥራቱ እንደድሮዎቹ አዝማቾች (ገዥዎች) ጌትነት ባለመፈለጌ ልባቸው እየታዘበ አመሰገኑኝ።

ሌሉ አዲሱን የአውራጃ ሞዴል አስተዳደር ሕዝቡ እንደወደደው ይገልጻሉ።

ይህ በአሰበ ተፈሪ የታየው «የአውራጃ አስተዳደር ሞዴል» ዐላማ ኖሮት፣ ዕቅድ ወጥቶለት፣ ቅደም ተከተል ተበጅቶ፣ የጊዜ ሰሌዳ ተሠርቶ፣ ለመሥሪያ ቤቶች የሥራ መመሪያ ደንብ ወጥቶ፣ በመሥራትና በማሠራት የተገኘው ውጤት፣ እንኳን በዚያን ጊዜ ዛሬም ያልተደረሰበት፣ በጣም ዘመናዊ የአስተዳደር ጅምር ነበር ማለት ይቻላል። እውነትም ወደ ሌሎች አውራጃዎች ቢሸጋገር ሊያስገኝ የሚችለው ጠቀሜታ ታምኖ፣ ሌላ እንደዚህ ያለ ሞዴል አውራጃ በሚዛን ተፈሪም የአውራጃ የራስ ገዝ አስተዳደር በአፈንጉሥ (በኋላ ደጃዝማች) ዘውዴ አየለ ከእንግሊዛዊ አማካሪ ጋር ሥራው እየተሞከረ ሳለ በኢጣሊያ ወረራ ተደናቀፈ።[10]



ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም

ካጥሩ አማሟት ገዳዩን ያስመሰግናልካ እንዲሉ የጨርጨር አውራጃ አስተዳደር ማማር መጀመሪያ ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያትንና በሳቸው የተመሩትን የሥራ ባልደረቦች፣

[10] በዚያን ጊዜ የአሰበ ተፈሪ ከተማ ሹም የነበሩት ቢትወደድ ዘውዴ ገብረሕይወት



ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም

ቀጥሎም የተተኩትን ሐኪም ወርቅነህንና የሥራ ባልደረቦቻቸውን ብቻ ሳይሆን፤ እንዲህ ያለ ውጤት ለማየት ጓጉተው ተጨንቀውና ተጠብበው እነዚህን ሰዎች መርጠው የሾሙትን እንደራሴና አልጋ ወራሹን ራስ ተፈሪን (በኋላ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴን) የሚያስመሰግን ጅምር ነበር።



*ሐኪም ወርቅነህ እሸቴ*



ሐኪም ወርቅነህ እሸቴ